# የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
# 2014 በጀት ዓመት የሴክተር ዕቅድ

ጥቅምት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ........................................................................ገጽ


መግቢያ ........................................................................ 5
የኢትዮጵያ ራዕይ ........................................................................ 6
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ ........................................................................ 6
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ ........................................................................ 6
እሴቶች ........................................................................ 6
ክፍል አንድ ........................................................................ 7
ያለፈው ዓመት እቅድ አፈፃፀም ግምገማ ........................................................................ 7
1.1 የሴቶች፣ የህፃናትና ወጣቶች ዘርፍን በተመለከተ ........................................................................ 7
1.2 የማህበራዊ ደህንነት ልማት ዘርፍ አፈፃፀምን በተመለከተ ........................................................................ 11
ክፍል ሁለት ........................................................................ 16
2.1 የልማት እቅዱ ቁሳዊና ሰብአዊ አቅሞች ........................................................................ 16
2.2. የልማት እቅዱ መነሻዎች ........................................................................ 16
2.3. የልማት እቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........................................................................ 17
2.4. የልማት እቅዱ የትኩረት መስኮች ........................................................................ 17
ክፍል ሶስት ........................................................................ 20
የ2014 በጀት ዓመት እቅድ ዓላማ፣ ግቦች፤ ዉጤቶች እና ተግባራት፤ ........................................................................ 20
3.1 የልማት እቅዱ ዓላማ ........................................................................ 20
3.2. የ2014 በጀት ዓመት የ9 ወር እቅድ ግቦች፣ ውጤቶችና ተግባራት ........................................................................ 20
I. የሴቶች ዘርፍ ........................................................................ 20
ግብ 1፡- የሴቶች መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ፤ ........................................................................ 20
ዉጤት 1፡- መብታቸው የተረጋገጠ ሴቶች፤ ........................................................................ 20
ዉጤት 2፡- ደህንነታቸው የተጠበቀ ሴቶች፤ ........................................................................ 20
ግብ 2፡ የሴቶች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ ........................................................................ 22
ውጤት 1፡- ተሳትፎአቸው የተረጋገጠ ሴቶች፤ ........................................................................ 22
ውጤት 2፡- ውክልናቸው የተረጋገጠ ሴቶች፤ ........................................................................ 22
ግብ 3፡- የሴቶች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ........................................................................ 23
ውጤት 1፡- ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ሴቶች ........................................................................ 23
ውጤት 2፡- ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ሴቶች ........................................................................ 24
ግብ 4፡ የሴቶች ተቋማዊነትና የተጠያቂነት ስርዓት ማጎልበት ........................................................................ 25
ውጤት 1፡- የሴቶች ማካተትና ተቋማዊነት፣ ........................................................................ 25
ዉጤት 2፡- የተዘረጋና የተጠናከረ የአሰራር ስርዓት/የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም፤ 25

II. የህጻናት ዘርፍ ........ 26
ግብ 1፡- የህፃናት መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማረጋገጥ፣ ........ 26
ዉጤት 1፡- የተረጋገጠ የሕጻናት መብት ........ 26
ዉጤት 2፡- የተረጋገጠ የሕጻናት ደህንነት፤ ........ 27
ግብ 2፡ የህጻናትን ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ ........ 29
ውጤት 1፡ የተረጋገጠ የህጻናት ተሳትፎ፣ ........ 29
ግብ 3፡- የህጻናትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ........ 29
ዉጤት 1፡- የተረጋገጠ የሕጻናት ማህበራዊ ተጠቃሚነት ........ 29
III. በወጣቶች ዘርፍ ........ 31
ግብ 1- የወጣቶች መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማረጋገጥ፤ ........ 31
ውጤት 1፡- መብታቸው የተረጋገጠ ወጣቶች፤ ........ 31
ዉጤት 2፡- ደህንነታቸው የተጠበቀ ወጣቶች፤ ........ 32
ግብ 2፡ የወጣቶች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ፣ ........ 33
ውጤት 1፡ ተሳትፎአቸው የተረጋገጠ ወጣቶች ........ 33
ውጤት 2፡ ውክልናቸው የተረጋገጠ ወጣቶች ........ 34
ግብ 3፡- የ ወጣቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ........ 34
ውጤት 1፡- ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጡ ወጣቶች፤ ........ 34
ውጤት 2፡- ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ወጣቶች ........ 35
ግብ 4፡- የተቋማትን ተቋማዊ ብቃት ማሳደግ ........ 37
ውጤት 1፡- የጎለበተ የመፈፀምና ማስፈጸም አቅም ........ 37
IV. የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ፣ ........ 38
ግብ 1. የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ ........ 38
ውጤት 1፡ የተደራጁና ወደ ሥራ የገቡ ምክር ቤቶች፣ ........ 38
ግብ 2. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ቤተሰቦችን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ እና ኑሮ ሁኔታ በማሻሻል ከድህነት እንዲወጡ ማድረግ፣ ........ 40
ውጤት 1፡ ማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ተጠቃሚነታቸው የጨመረ በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት የታቀፉ ድሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፤ ........ 40
ግብ 3፡ የኢኮኖሚያዊ እና የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፤ ........ 41
ውጤት 1፡ የኢኮኖሚያዊ እና የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ይጨምራል፣ ........ 41

ግብ 4፡ የአቅም ግንባታ፣ የግንዛቤ እና አድቮኬሲ ሥራዎችን በማስፋፋት የአረጋዊያንን ሁለንተናዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ ........ 45

ውጤት 1፡ ተጠቃሚ የሆኑ አረጋዊያን፤ ........ 45

ግብ 5፡ የተሃድሶ አገልግሎቶችን በማስፋፋት አረጋውያን ተገቢውን ድጋፍ እና እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ ........ 47

ውጤት 1፡ የተዘረጉ የተሀድሶ አገልግሎቶችና የተቋቋሙ አረጋውያን ........ 47

ግብ 6፡ የቅንጅት እና ትብብር ሥራዎችን በማጠናከር በተቋማት የኃላፊነት ክልል የአረጋውያንን ጉዳዮች ተፈጻሚነት ማረጋገጥ ........ 47

ውጤት 1፡ የተጠናከረ የቅንጅትና የትብብር ሥራዎች፣ ........ 47

ግብ 7፡ የአካል ጉዳተኞችን ተካታችነት፣ ተሳታፊነት፣ ተደራሽነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ ........ 48

ውጤት 1፡ ተጠቃሚ የሆኑ የአካል ጉዳተኞች፣ ........ 48

ግብ 8፡ የሴክተሩ ሙያተኞችና በዘርፉ የሚንቀሳቀሱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ብቁ በማድረግ የሴክተሩን ተልዕኮ ማሳካት፣ ........ 52

ውጤት1፡ ተደራሽነቱ ያደገ የማህበራዊ ጥበቃ አገልገሎቶችን፤ ........ 52

ዋና ዋና አስተዳደራዊ ስራዎች ........ 53

የህግ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት ........ 53

የተቋሙን ፋይናንስ አጠቃቀምን ማሳደግ ........ 53

የእቅድ ትግበራ ስራ አመራር ስርዓትን ማሳደግ፤ ........ 53

የመረጃ ፍሰት በማዘመን ተደራሽነትን ማሳደግ ........ 54

የሰው ሃብት ልማትን ማጎልበት ........ 55

የህዝብ ግንኙነት፣ ኮሙኒኬሽን ሥራዎችንና የመረጃ ፍሰትን ተደራሽነትን ማሳደግ፣ ........ 55

የኦዲት አገልግሎት ማከናወን ........ 55

የሪፎርም ሥራን መከታተልና መገምገም፣መደገፍ ........ 56

የሥነ ምግባር እና ጸረ-ሙስና ተግባራትን መከታተል ........ 56

የንብረት አቅርቦትና የጠቅላላ አገልግሎት ድጋፍ መስጠት ........ 56

የእቅዱ ማስፈጸሚያ ስልቶች ........ 57

የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረ መልስ ስርአት ........ 58

ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችና ሊወሰዱ የሚገባቸው መፍትሄዎች፣ ........ 59

መልካም አጋጣሚዎች ........ 59

ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች/ ስጋቶች ........ 59

መወሠድ ያለባቸው እርምጃዎች፡ ........ 60

ማጠቃለያ ........ 60

## መግቢያ

የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴርና የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለፉት አመታት እንደ ሴክተር በርካታ አበረታች የልማት ውጤቶችን ማስመዝገብ ችለዋል:: በዚህ ሂደት ውስጥ ከሀገራችን ህብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖሊቲካዊ መስኮች ያላቸውን ተሳታፎ እና ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ እንዲሁም የህፃናትን መብትና ደህንነት በማስጠበቅ በተከናወኑት ተግባራት ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

ሆኖም የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖሊቲካዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ሙሉ በሙሉ ከማሳካት አንጻር አሁንም በርካታ ክፍቶች ይስተዋላሉ፡፡ ይህም በማስፈፀም ሂደት ከአደረጃጀት፣ ከአሰራር፣ ከሰው ኃይል ልማት እንዲሁም ከቅንጅትና ህብረ-ኃይልን ከማሳደግ አንፃር በተጨማሪም ዘርፉን በቁሳቁስና በበጀት ከማጠናከር አንፃር የተከናወኑት ተግባራት ዝቅተኛ መሆንና የሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን አደረጃጀቶች ነፃና ሞጋች አለመሆናቸውና አለመጠናከራቸው በመስኩ የተመዘገቡ ውጤቶች በሚፈለገው መጠን አለመሆናቸው ማሳያ ናቸው፡፡

እነዚህ የታዩ ተግዳሮቶችን ከግምት በማስገባት በቀጣይ የልማት እቅድ ዘመን ችግሮቹን በዘላቂነት በመቅረፍ የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁለንተናዊ መብትና ደህንነት ለማስጠበቅና ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖሊቲካዊ መስኮች ያላቸውን ሚና ለማሳደግ የ2014 ዓመት የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

ዕቅዱ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን በክፍል አንድ ያለፉት ዓመታት ዕቅድ አፈፃፀም ጠቅለል ባለ መልኩ እና የተለዩ ክፍተቶችና ተግዳሮቶች ቀርበዋል፡፡ በክፍል ሁለት የልማት እቅዱ መነሻዎች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የትኩረት መስኮች እና ዓላማዎች የልማት ዕቅዱ ዋና ዋና ግቦች፣ የልማት እቅዱ ማስፈፀሚያ ስልቶች እና የክትትልና ግምገማ ስርዓት በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ራዕይ

ሀገራችን በ2022 የአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት ሆና ማየት፤

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ

በ2022 ዓ/ም የዜጎች እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተረጋገጠባትና የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች የተስፋፉባትን የበለጸገች ኢትዮጵያን ማየት፡፡

በ2022 ዓ/ም የሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን እኩል ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት፤ የስርዓተ-ፆታ እኩልነት፣ የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች የተረጋገጠባት፣ የህጻናት መብት እና ደህንነት የተከበረባት የበለጸገች ኢትዮጵያን ማየት፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ

- የሴቶችንና የወጣቶችን እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ የህፃናትን መብትና ደህንነት ማስጠበቅ እና የፆታ ዕኩልነትን ማስፈን፣ ዜጎች የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት (የአካል ጉዳተኞች እኩል እድልና ሙሉ ተሳታፊነት እንዲረጋገጥ፣ አረጋውያን ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙና ተሳትፎአቸው እንዲጎለብት፣ በልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ምክንያት በድህነት ተጋላጭነትና መገለል ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች የተለያዩ ድጋፎችን) እንዲያገኙ ማድረግ፣

## እሴቶች

- የህግ የበላይነትን ማስከበር
- ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን
- ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት
- መልካም ሥነ-ምግባር
- የቡድን ስራን ማበረታታት፤
- ፍትሀዊነት

# ክፍል አንድ

## ያለፈው ዓመት እቅድ አፈፃፀም ግምገማ

### 1.1 የሴቶች፣ የህፃናትና ወጣቶች ዘርፍን በተመለከተ

የሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል ከላይ እስከ ታች ድረስ 8,603,106 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ በመፍጠር 1,794 ቀበሌዎች ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በፌዴራል ደረጃ የብሄራዊ የጥቃት አስወጋጅ ግብረ ሃሎችን ከማጠናከር አንጻር 4,439 ጥምረቶችን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡

ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች በተቋቋሙ የተሃድሶ አገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት 4,816 ሴቶች ወደ ተሀድሶ መስጫ ማዕከላት ገብተው የተለያዩ የስነ ልቦና እና ማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

ጥቃት ለደረሰባቸዉ ሴቶች የአንድ መስኮት አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ በታቀደው እቅድ መሰረት 5 የአንድ መስኮት አገልግሎት በማቋቋም 4,816 ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤ ሴቶች አደጋ ከመድረሱ በፊት እና ከደረሰ በኋላ ችግሮችን የሚያሳዉቁበት ነፃ የስልክ ጥሪ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ በታቀደው እቅድ መሰረት 3 ባለ አራት ዲጂት የነጻ ስልክ መስመር በመዘርጋት 32,450 ለሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ በመፍጠር ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡

በሴቶች በሰላም ተሳትፎ ዙሪያ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱና እንዲሳተፉ ከማድረግ አንጻር 876,914 ለሰላም የሴት አምባሳደሮች በሰላም ዙሪያ ለሚሰሩ ሴት አመራሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በሃገር አቀፍ ደረጃ ሴቶች በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የንቅናቄ እቅድ በማዘጋጀት ከ 4.3 ሚሊዬን በላይ ሴቶች በአካባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለዉጥ እና በሌሎች ተግባራት እንዲሳተፉ ማድረግ ተችሏል፡፡

በየደረጃው የሴቶችን አቅም በመገንባት ለአመራር ብቁ የሆኑ ሴቶችን ፑል ከመፍጠር አንጻር የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠትና የአመራር ብቃታቸውን በማሳደግ 4,762 የሚሆኑ ሴቶች ለአመራርነት ብቁ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም መሰረት በሀገር አቀፍ ደረጃ በአስፈጻሚ አካላት 50 በመቶ፣ በህግ ተርጓሚ ደረጃ 26.6 በመቶ እንዲሁም በህዝብ በተወካዮች ምክር ቤት ደረጃ 20 በመቶ እንዲሁም በስራ አስፈጻሚ ደረጃ 38.8 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅም ከማሳደግ አንጻር ሴቶች ብድር አግኝተው በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በታቀደው እቅድ መሰረት 600,365 ሴቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

ሴቶች የቁጠባ ባህላቸው እንዲዳብር እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ከማሳደግ አንጻር በ2013 ዓ.ም 3.2 ሚሊዬን ሴቶች 470,285,786 ብር  እንዲቆጥቡ ማድረስ ተችሏል፡፡ ሴቶች በሕብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 359,258 ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

የገጠር ሴቶችን የመሬት የባለቤትነት መብትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት 563,530 ሴቶችን የመሬት ባለቤትነትና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥላቸው ማድረግ ተችሏል፡፡ የሴቶችን የስራ ጫና ለማቃለል ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት 903,406 ሴቶች የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ተችሏል፡፡

በመንግስት መ/ቤቶች ያለውን የተንከባካቢ ባለሙያዎች ዕጥረት ለመቀነስ ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር በፌዴራል ሴክተሮች በስራ ላይ የሚገኙ 56 ተንከባካቢዎችን መሰረታዊ የእንክብካቤ ስራ ላይ የ6 ወር ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

በተለያዩ የፌደራል እና የክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር 36 የህጻናት ማቆያዎች በማቋቋም 10,651 ህፃናት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከጠቅላላ ሴት የመንግስት ሰራተኞች የከፍተኛ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ሴት የመንግስት ሰራተኞች ድርሻ ለማሳደግ በመጀመሪያ ዲግሪ 7፣ 122 ሴቶች በሁለተኛ ዲግሪ በአጠቃላይ 129 ሴቶች እና 9 ሴቶችን የስኮላር ሺፕ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

በአዳሪ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሴት ተማሪዎች ድጋፍ ከማድረግ አንጻር 5,439 ለሚሆኑ ሴት ተማሪዎች ድጋፍ በማድረግ ከእቅድ በላይ ማሳካት ተችሏል፡፡

ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን ለ5,000,000 ሴቶች በጎልማሶች ትምህርት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 601,867 ሴቶችን በጎልማሶች የትምህርት ፕሮግራም ተጠቃሚ ተደርገዋል፡፡

ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር 1,628,033 ሴቶች የጡትና የማህጸን ካንሰር ቅድመ ምርመራ ሴቶች ምርመራ እንዲያደርጉ ማድረግ ከዚህም ውስጥ 15,730 ሴቶች ህመሙ ተገኝቶባቸዉ ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ 78 የማህጸን መውጣት ችግር ላጋጠማቸው ሴቶች የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተችሏል፡፡

ህጻናት የልደት የምስክር ወረቀት እንዲያገኙና የህጻናትን የልደት ሰርተፊኬት ተደራሽነት ለማሳደግ ከኢሚግሬሽንና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት 1,335,672 ህጻናት እንዲመዘገቡ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የህጻናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በህግ የህፃናት አባትነትን እንዲረጋገጥ ከማድረግ አንፃር 86 ህጻናት አባትነት እንዲረጋገጥላቸው ማድረግ ተችሏል፡፡

በህፃናት መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ የብዙሀን መገናኛዎችን፣ መድረኮች እና ልዩ ልዩ ኩነቶችን በመጠቀም በተሰራው ስራ 29,979,965 ህብረተሰብ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጥ ተችሏል፡፡

በሀገር ውስጥ አማራጭ ፕሮግራሞች ከማድረግ አንጻር በማህበረሰብ አቀፍ የህፃናት ድጋፍና ክብካቤ  804,742፣ በተቋማት የ1% ስፖንሰርሺፕ ድጋፍ 128,122 ህፃናት፣ በፎስተር ኬር 3,241 ህፃናት እንዲሁም በጉዲፈቻ 1,232 ህፃናት በድምሩ 937,337 ህጻናት ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

የህጻናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በጎዳና ላይ ያሉና ከስደት ተመላሽ የሆኑ ህጻናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በተያዘው እቅድ መሰረት 11,427 ህፃናት

ከቤተሰቦቻቸውና ህብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉና እንዲዋሀዱ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ 4 የሆት ላይን፣ 9 የአንድ መስኮት ማእከላትን በማቋቋም 4,589 ህፃናት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

በልዩ ድጋፍ የሚሹ 7,865 ህፃናትን በልዩ ድጋፍ መደገፍ የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም 572 የሚሆኑ ከወላጆቻቸው ጋር በማረሚያ ቤት ያሉ ህፃናት በተለያዩ አማራጭ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

የህጻናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ እና ደህንነታቸውን ከማስጠበቅ አንጻር 20,512 የህጻናት ቤተሰቦች የማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ድጋፍ እንዲገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ 1680 የሚሆኑ የህፃናት የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶችን በአዲስ የመቋቋምና 2178 ጥምረቶችን የማጠናከር ስራ መስራት ተችሏል፡፡

የህፃናት መጫወቻና መዝናኛ ስፍራዎችን ለማቋቋም በተያዘው እቅድ መሰረት 2 ምቹ የህፃናት ስፍራዎችን በአዲስ አበባና ደቡብ ክልል በማቋቋም 106,522 ህፃናት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

የህጻናትን ተሳትፎ ከማሳደግ አንጻር 2,500 የህጻናት ፓርላማዎችን እስከታች ድረስ ማለትም በቀበሌ 239፣ በወረዳ 98 ፣ እንዲሁም በክልል 2 ፓርላማዎች በድምሩ 339 ፓርላማዎች እንዲቋቋሙ ማድረግ የተተቻለ ሲሆን በተጨማሪም 12,337 ፓርላማዎችን ማጠናከር ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ 35180 ህጻናት በህዝብ ም/ቤቶች እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ 8650 የህፃናት ፓርላማ ተወካዮች በህዝብ ም/ቤቶች እንዲሳተፉ ማድረግ ተችሏል፡፡

ዓለም አቀፍ የህፃናት ቀንን በማስመልከት በየደረጃው በሚካሄዱ ፕሮግራሞች 3,381,791 ህፃናት እንዲሳተፉና ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

የወጣቶችን ተሳትፎ በክረምትና በበጋ የበጎ ፍቃድ ከማሳደግ እና በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የተሰማሩ ወጣቶች ድርሻ ከማሳደግ አንጻር 22.7 ሚሊዮን ወጣቶች በማሳተፍ ከ 53.5 ሚሊዮን በላይ የህብረተሰብ ክፍል በአገልግሎቱ እንዲጠቀሙ በማድረግ 9.4 ቢሊዮን ብር የሚገመት ወጪ ማዳን ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ በ2013 በጀት 1.7 ሚሊዬን አዳዲስ ወጣቶችን በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ የወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ተችሏል፡፡ በየደረጃው በዚህ ተግባር ተሰማርተው የላቀ አስተዋፆ ላበረከቱ 51,077 ለሚሆኑ ወጣቶች የማበረታቻና እውቅና የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡

የወጣቶችን የቁጠባ ባህል እንዲዳብርና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ከማሳደግ አንጻር 2.32 ሚሊዬን ወጣቶች 2.798 ቢሊዬን ብር እንዲቆጠቡ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ የወጣቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር 586,853 ወጣቶች 5,604,672,963 ቢሊዬን ብር የብድር አገልገሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ወጣቶች አቅም ለማሳደግ፣ ክህሎታቸውን የበለጠ እንዲያዳብሩ ለማድረግ 456,423 በስራ እድል ፈጠራ ክህሎት፣ በራስ መተማመንና ተያያዥ ጉዳዮች ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል፡፡

በሁሉም የአገሪቱ 131 አዳዲስ የስብዕና ልማት ማዕከላት በመገንባት፣ 146 ማእከላት እንዲጠናከሩ ማድረግና 137 የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲኖራቸው በማድረግ 23.7 ሚሊዬን ወጣቶች በማዕከላቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎች ተከናውኗል፡፡

የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማሳደግ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ፣ ከስራ ዕድል ፈጠራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ወጣቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲደራጁ በማድረግ ለ1,871,870 ወጣቶች በተለያዩ መስኮች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል፡፡

ወጣቶች በአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዲሳተፉና እንዲሁም በአካልና በስነ ልቦና ጤናማ የሆነ ወጣት ከመፍጠር አንጻር በየደረጃው በተካሄዱ የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎች 6,936,700 የሚሆኑ ወጣቶች በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ ተከናውኗል።

486,025 ወጣቶች የህይወት ክሎት ስልጠናዎችን መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ 189,198 ለሚሆኑ ወጣቶች በማረሚያ ቤት ለሚኖሩ ታራሚዎች በተለያዩ በተለያዩ ሙያዎች የክህሎት ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡

## 1.2 የማህበራዊ ደህንነት ልማት ዘርፍ አፈፃፀምን በተመለከተ

ብሄራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርዓት /MIS/ ለማጠናከር የሚያስችል ራሱን የቻለ አንድ የሥራ ክፍል እንዲኖረው ረቂቅ ሰነድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት በአገሪቱ የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርዓት /MIS/ አደረጃጀትና

መዋቅር ያላቸውን የውስጥና የውጭ አገር ተቋማት ልምድ እና ተሞክሮ በመውሰድ የሥራ ክፍሉን ለመዋቅርና የሥራ መዘርዝር በረቂቅ ደረጃ ሰነዱ ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋመው የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት የሚመራበት ረቂቅ መመሪያ ለማዘጋጀት እና ክልላዊ ምክር ቤቶችን ለሚያቋቁሙ ክልሎች ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት በታቀደው መሠረት በፌዴራል ደረጃ የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት ሲቋቋም ምክር ቤቱ የሚመራበት መመሪያ ረቂቅ ሰነድም ተዘጋጅቷል፡፡ ወደፊት የሚቋቋመውን የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤትን ሥራ በጊዜያዊነት ተክቶ የሚሰራ የተለያዩ የመንግስትና የልማት አጋሮችን ተቋማት በአባልነት የያዘ ብሄራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፕላት ፎርም ተቋቁሞ የማህበራዊ ጥበቃ አደረጃጀቶችን አሠራሮችን ለማጠናከር የሚያግዙ ሥራዎች ተከናውኗል፡፡

ለመንግሥት የቀረቡትን ሦስት አዋጆች (የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ፣ የማህበራዊ ጥበቃ ካውንስል ማቋቋሚያ እንዲሁም ምንም የገቢ ምንጭ የሌላቸው አረጋውያን የመሠረታዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል) እንዲፀድቁ ለመከታተል በታቀደው መሠረት የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውይይት ከመቅረቡ በፊት በገንዘብ ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሰጥበት ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት አዋጁ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበት ሚኒስቴር መ/ቤቱ አዋጁ ለሚኒስትሮች ምክርቤት ቀርቦ ቢጸድቅ የበርካታ ድሃና ተጋላጭ ዜጎችን ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመተግበር እንደሚያግዙ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ስለሆነም ሦስቱም ሰነዶች በተያዘው በጀት ዓመት ፀድቀው ሥራ ላይ እንዲውሉ ክትትል ተደርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የማህበራዊ ዘርፉን የመፈፀም አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ 7 ሰነዶችን በረቂቅ ደረጃ ለማዘጋጀት እንዲቻል ተዛማጅ መረጃዎችና የሌሎች አገሮች ተሞክሮዎችን በመዳሰስ በረቂቅ ደረጃ ሰነዶቹ ተዘጋጅተዋል፡፡

በ11 ከተሞች የሚገኙ ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ የሆነ ዜጐች ለማቋቋም ውል የገቡ 44 የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት በገቡት ውል መሠረት አገልግሎቱን እየሰጡ ስለመሆናቸው በየሩብ ዓመቱ የመስክ ምልከታ በማድረግ ለመደገፍ፣ ለመከታተልና ለመቆጣጠር እና ስለአፈፃፀማቸው ግብረ-መልስ ለመስጠት በተደረገው ሂደት በህፃናት ዘርፍ ውል ከገቡት 27 ተቋማት ውስጥ 24ቱ 4,159 ህፃናትን ከጎዳና በማንሳት ተጠቃሚ እያደረጉ እንደሆነ በተደረገው ክትትል ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ 2,028 ህፃናትን ከቤተሰብ ጋር

የማቀላቀል እንዲሁም 2,121 ህፃናት በጊዜያዊ መጠለያዎች አገልግሎት እንዲያገኙ 915 ያህል ህፃናት ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ከፕሮግራሙ ማቋረጣቸውን በክትትልና ቁጥጥር ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የልዩ ድጋፍ አገልግሎት ዘርፎች (ወጣቶች/ጎልማሶች፣ ህፃናት የያዙ እናቶች እና አረጋዊያን) አገልገሎቱን ለመስጠት ፍላጎታቸውን ከገለፁ 31 ተቋማት ውስጥ መስፈርቱን ካሟሉ 17 ድርጅቶች ጋር በድምሩ 5,550 ዜጐችን (3,203 አረጋዊያን፣ 1,380 ህፃናት ያላቸው እናቶችን እና 967 ወጣቶችን) ተጠቃሚ ለማድረግ የውል ስምምነት መፈራረም ተችሏል፡፡የውል ስምምነቶችን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ በተደረገ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ውል ከገቡት ተቋማት ውስጥ የቅድመ ዝግጅት ስራቸውን ያጠናቀቁ ስምንት ተቋማት ወደ ሥራ በመግባት 2,607 አረጋዊያን፣ 211 ህፃናት የያዙ እናቶች፣ 171 ወጣቶችን በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ማድረጋቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከጎዳና ተነስተው በጊዜያዊ መጠለያ አገልግሎት እያገኙ ያሉ ዜጎች ላይ የኮሮና ቫይረስ ያሳደረውን ተፅዕኖ ለመከላከል እንዲቻል ከዩኒሴፍ በተገኘ 4,831,569 ብር ምግብ እና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ተገዝቶ ለ22 አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ 3,581 (77%) የእንክብካቤ ጥምረቶች እንዲቋቋሙ ሲደረግ 5,533 የእንክብካቤ ጥምረቶችን ድጋፍ በማድረግ ከዕቅድ በላይ እንዲጠናከሩ ተደርጓል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ በ137 (የዕቅዱ 68%) አዲስ የአረጋዊያን እና 817 አዲስ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ከዕቅድ በላይ እንዲቋቋሙ ድጋፍ ሲሰጥ ቀድሞ የተቋቋሙ 745 የአረጋዊያንና 1,366 የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ከዕቅድ በላይ እንዲጠናከሩ የስልጠናና የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

በሀገራችን በሚገኙ ዋና ዋና ከተሞች በከፋ ድህነት ውስጥ የሚገኙት 60,336 አረጋዊያን እና 3,599 ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሥነ-ልቦናና ማህበራዊ ተሃድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ በታቀደው መሠረት ለ41,068 (8,393 ወንድና 9,557 ሴትና በፆታ ያልተለየ 35,512) አረጋዊያን እና ለ25,741 (7,220 ወንድና 5,441 ሴት እና በፆታ ያልተለየ 13,080) ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሥነ-ልቦናና ማህበራዊ ተሃድሶ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ለበጀት ዓመቱ የተያዘው ተግባር እንደቅደም ተከተላቸው 68% እና ከዕቅድ በላይ ተፈፃሚ ተደርጓል፡፡

ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በድህነት ውስጥ ከሚገኙት መካከል 42,326 አረጋውያን፣ 10,899 ውሎና አዳራቸው ጎዳና ያደረጉ እና 27,883 አካል ጉዳተኞች የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የትምህርት፣ የስልጠና እና የሥራ ስምሪት ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ በታቀደው መሠረት በአምስት ክልሎች (አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝና ደ/ብ/ብ/ህ) እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ለ125,328 (3,302 ወንድና 3,105 ሴትና በፆታ ያልተለየ 118,921) አረጋውያን እና ለ8,204 (1,260 ወንድና 859 ሴትና በፆታ ያልተለየ 6,085) ውሎና አዳራቸው ጎዳና ያደረጉ እና 13,850 (2,472 ወንድ፣ 1,864 ሴትና 9,514 በፆታ ያልተለየ) አካል ጉዳተኞች ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም የሥራ ስምሪት ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳትፎአቸው እንዲያድግ ተደርጓል፡፡

ማህበረሰብን መሠረት አድርገው የተዋቀሩ አደረጃጀቶች፣ ሲቪክ ማህበራት እና የንግዱ ማህረሰብ በማስተባበር ለ4,324 አረጋዊያን፣ 2,499 ውሎና አዳራቸው ጎዳና ያደረጉ እና 13,405 አካል ጉዳተኛ የሆኑ ዜጎች የድጋፍ እና የእንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ በማድረግ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በታቀደው መሠረት ለ127,102 (3,961 ወንድና 5,890 ሴትና በፆታ ያልተለየ 117,251) አረጋውያን እና ለ14,405 (1,722 ወንድና 867 ሴትና በፆታ ያልተለየ 11,816) ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ ያደረጉ እና 7,492 (646 ወንድ፣ 517 ሴት እና 6,392 በፆታ ያልተለየ) አካል ጉዳተኛ የሆኑ ዜጎች እንክብካቤ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም አፈፃፀማቸው እንደቅደም ተከተላቸው ከዕቅድ በላይ እና 56%ቱ ተፈፃሚ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ የተሰጡ ድጋፎች ከዕቅድ በላይ ተግባራዊ ሊደረጉ የቻሉት በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት በርብርብ መሥራት በመመቻቹ ነው፡፡ ይሁንና አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ የሆኑትን ትኩረት በመስጠት በቀጣይ ሊሠራ ይገባል፡፡

የአካል ጉዳተኞች የእንቅስቃሴ ችግር ለማቃለል ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ከታክስ ነፃ ለማስገባት እንዲችሉ መስፈርቱን ላሟሉ ለ393 (323 ወንድ እና 70 ሴት) አካል ጉዳተኞች የመብቱ ተጠቃሚ ተደርገዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለተ.መ.ድ የምታቀርበውን ሁለተኛውን አካል ጉዳተኞች መብት አጠባበቅ ኮንፌንሽን አፈፃፀም የተመለከተ አገራዊ ሪፖርት ለማዘጋጀት የሚረዳ ሀብት ከኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን ጋር በጋራ በመሆን ፕሮጀክት ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ከCBM የብር 600,000 ድጋፍ በማግኘትና አማካሪ በመቅጠር ሪፖርቱ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ከፊንላንድ መንግስት በተገኘ ድጋፍም ከኢትዮጵያ አካል

ጉዳተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር በፌዴሬሽኑ የሚተገበርና በሚኒስቴር መ/ቤታችን ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር የሚደረግበት አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የብር 14 ሚሊዮን (በአራት ክልሎች የሚተገበር) የሁለት ዓመት የፕሮጀክት ስምምነት ተፈርሞ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተገብቷል፡፡ ሂዩማኒቲ ኤንድ ኢንክሉዥን እና ኢትዮጵያን ሴንተር ዲሴቢሊቲ ኤንድ ዴቨሎፕመንት እና ብርሃን ለህፃናት ከተባሉ አካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰሩ መ.ያ.ድ.ች ጋር ከብር 100 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ፕሮጀክቶች ስምምነት በመፈራረም የድጋፍና ክትትል ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የልማት አጋሮችን በማሳመን ለአካል ጉደተኞች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት በአማካሪነት የሚሰራ አንድ ባለሙያ ለሁለት ዓመት መቅጠር የሚያስችል የ48 ሺህ ዶላር ስምምነት በመፈራረም ባለሙያ ለመቀጠር ማስታወቂያ ወጥቶ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በገጠርና በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በታቀፉ ክልሎችና የፌዴራል ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ 1,193,448 የገጠርና 93,120 የከተማ በድምሩ 1,286,568 ዜጎች የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ዕቅዱ ተፈፃሚ ተደርጓል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2.1 የልማት እቅዱ ቁሳዊና ሰብአዊ አቅሞች

**ሰብአዊ አቅም**

ለዕቅዱ መሳካት የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ዙሪያ ላይ የተሰማሩ የተለያዩ አደረጃጀቶች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ምሁራን፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ በጎ ፈቃደኛ ግለሰቦች፣ ህብረተሰቡ እና የግሉ ሴክተር ተሳትፎ የዘርፉን የልማት ዕቅድ ለማሳካት አቅሞች ይሆናሉ፡፡

**ቁሳዊና የፋይናንስ አቅም**

የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎና ተጠቃሚነት በተሟላ ሁኔታ ለማስጠበቅ በሚደረገው ጥረት ልዩ ልዩ የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን፣ ከተለያዩ አካላት ድጋፍ፣ እንክብካቤና ጥበቃ በአይነትና በገንዘብ የተሰበሰቡ ቁሳዊ ሀብቶችን፣ በዘርፉ ለማሰማራት ፍላጎት ያላቸው በርካታ ተራድኦ ድርጅቶች መኖር፤ ለሥራዎች ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እና በጀት ለማሰባሰብ የሚያግዙ ሥርዓቶች፣ የቅንጅትና ትብብር አሰራሮችን እና በዚህም ለሚገኙ ቁሳዊና የፋይናንስ አቅሞች የዘርፉን የልማት ዕቅድ ግቦች መሳካት በርካታ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል፡፡

## 2.2. የልማት እቅዱ መነሻዎች

የአስር ዓመቱን የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት ሂደት ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ የተለመችው ራዕይ፣ የምዕተ ዓመቱ የዘላቂ ልማት ግቦች፣ ቀጣናዊ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች፣ የስነ-ህዝብ ትንበያዎች፣ የመጀመሪያውና የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች፣ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች አካል ጉዳተኞች አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የተመለከቱ የኢኮኖሚ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መስኮች ለተቋሙ በአዋጅ የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንዲሁም 2013 በጀት ዓመት የስራ አፈፃፀም ወቅት የተገኙ ተሞክሮዎችና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እንደመነሻ ተወስደዋል፡፡

### 2.3. የልማት እቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች

የልማት ዕቅዱ በዋናነት መብት /Right/፣ መወከል /Representation/፣ ሀብት /Resource/፤ እንዲሁም ተጠያቂነት /Responsiblities/ ያማከለ የሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫዎች ይኖሩታል፡፡

- ❖ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓትን በሀገር አቀፍ ደረጃ በመዘርጋት በየጊዜው ሽፋኑንና የጥራት ደረጃው እያደገ እንዲሄድ ይደረጋል፡፡
- ❖ የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎቶች አካታችና ተደራሽነትን በማሻሻል አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች አቅማቸውን ችሎታቸውን በመጠቀም አምራችና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርና በመቀናጀት የትምህርትና ስልጠና ዕድሎች እንዲመቻችላቸውና በማንኛውም የስራ መስክ እንዲሰማሩ ይደረጋል፤
- ❖ የሴቶች ህፃናት ወጣቶች አካል ጉዳተኞች አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች (ዜጎች) በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት ፍትሃዊ ተሳትፎ እና ዉክልና እንዲኖራቸው ማድረግ፤
- ❖ ዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማሳደግ የማሕበረሰቡ የአመለካከት ለውጥ ዙሪያ መስራት፣
- ❖ ዜጎች እኩል ተሳታፊ እና ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግና በሁሉም መስኮች ያላቸውን አይተኬ ሚና እንዲወጡና አስተዋፆ እንዲያበረክቱ ማስቻል፤

### 2.4. የልማት እቅዱ የትኩረት መስኮች

<u>ሴቶችን ማብቃት፣ የስርዓተ ፆታ እኩልነት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፡-</u> ሴቶች እኩል ዕድል የማግኘት መብታቸውንና ከማናቸውም ጥቃትና መድሎ ነፃ እንዲሆኑና በሁልም መስክ ተሳትፎአቸውን ለማጎለበት ያለመ ነው፡፡

<u>የህፃናት መብትና ጥበቃ፡-</u> በህፃናት ሁለንተናዊ ስብዕና ቀረፃ፣ ትርጉም ያለው የህፃናት ተሳትፎ ማሳደግ እንዲሁም የህፃናትን ጥበቃ ለማጠናከር የሚያስችል አደረጃጀት እና አሰራር መዘርጋት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

**<u>ወጣቶችን ማብቃት፤ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸው ማሳደግ፡-</u>** ወጣቶች ዕምቅ አቅምና ችሎታቸውን አውጥተው በመጠቀም በሁሉም መስኮች ተሳታፊ፣ ተወዳዳሪ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ ማድረግን ያካተተ ነው፡፡

**<u>የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶችን ጉዳይ ተቋማዊነት ማሳደግ፡-</u>**

በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የዜጎችን ጉዳዩን ተቋማዊ እንዲያደርጉ እንዲሁም የተቋማትን መፈጸምና የማስፈጸም አቅም በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

**<u>የማህበራዊ ጥበቃን ማጠናከርና ማስፋፋት፡-</u>** በማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ የተለዩ የትኩረት መስኮች (ማለትም ልማታዊ ሴፍቲኔትን ማስፋፋት፣ የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል፤ የማህበራዊ መድንን ማሰፋፋት፤ የመሠረታዊ አገልግሎት ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ እና ለጥቃትና በደል ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎች የሕግ ጥበቃ እና ድጋፍ መስጠት) ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግሰታዊ ያልሆኑ አካላትና የልማት አጋሮች ጋር በቅንጅትና በትብብር ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

**<u>የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎቶች አካታችነትና ተደራሽነትን ማሻሻል፡-</u>** የአካል ጉዳተኞችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተካታችነት ለማሳደግ የሚያስችሉ (እንደየጉዳት አይነታቸው ታሳቢ ያደረገ የአካልና አካል) ድጋፎች በቅረበት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ አረጋዊያንና አካል ጉዳተኞች አቅማቸውንና ችሎታቸውን በመጠቀም አምራችና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርና በመቀናጀት የትምህርት እና ስልጠና እድሎች እንዲመቻቹላቸው እና በማንኛውም የሥራ መስክ እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም አምራች ዜጎች በመሆን በሃገሪቱ በእድገት ጉዞም የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ አስፈላጊውን የሥነ-ልቦና እና ማህበራዊ ድጋፎች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በድርጅቶች አካል ጉዳት ያለባቸው ሠራተኞች በስራ ቦታ መገለልና መድሎ እንዳይደርስባቸው እንዲሁም በስራ ቦታ ተመጣጣኝ ማመቻቸትን /reasonable accomedation/ ስለመሟላታቸው በቁጥጥር እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

የጎዳና ተዳዳሪነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራት ተፈጻሚ ይደረጋሉ፡፡ የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃምን ለመቀነስ የሚያስችሉ የተሃድሶ አገልግሎቶች ይስጣሉ፡፡ የችግሩ ሰለባ የሆኑትን የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃሚዎች የማቋቋም ሽፋኑ እያደገ እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ በዋና ዋና ከተሞች የሚገኙትን የማህበራዊና

ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብተረሰብ ክፍሎች የመሠረታዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚነታቸው እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የ2014 በጀት ዓመት እቅድ ዓላማ፣ ግቦች፤ ዉጤቶች እና ተግባራት፤

### 3.1 የልማት እቅዱ ዓላማ

- ❖ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋትና አገልግሎቶችን በማስፋፋት ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ክፍሎች (ሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ) የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ እኩል ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

### 3.2. የ2014 በጀት ዓመት የ9 ወር እቅድ ግቦች፣ ውጤቶችና ተግባራት

**I. የሴቶች ዘርፍ**

**ግብ 1፡- የሴቶች መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ፤**

**ዉጤት 1፡- መብታቸው የተረጋገጠ ሴቶች፤**

<u>የሚከናወኑ ተግባራት</u>

- ❖ አዳዲስ የሴት አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ድጋፍ በማድረግና የተደራጁ 21,816 አደረጃጀቶችን በማጠናከር 5,700,019 ሴቶች መብትና ጥቅማቸውን እንዲያስጠብቁ ማድረግ፣

**ዉጤት 2፡- ደህንነታቸው የተጠበቀ ሴቶች፤**

<u>የሚከናወኑ ተግባራት</u>

- ❖ በተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ አደጋ እና ኮቪድ 19 ተጋላጭ ለሆኑ ለ 757,626 የማህበረሰብ ክፍሎች ሰብዓዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- ❖ በሚካሄዱ ኩነቶች በመጠቀም በስርአተ ጾታ እኩልነት፣ ጾታዊ ጥቃትንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመከላከልና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ለ9,361,350 ህብረተሰብ ግንዛቤ መፍጠር፣

- በሴቶች አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ ስነልቦናዊ ጥቃት እና በህፃናት ያለዕድሜ ጋብቻ ላይ በሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶች ዙሪያ የ12,498,810 የህረተሰብ ክፍሎችን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ ይሰራል፣
- በሴቶች ጥቃትና ጎጂ ልማዳዊ ደርጊቶች ዙሪያ ለ249,664 አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣
- 2 የብሄራዊ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀል አድራሾች ብሔራዊ መረጃ ስርዓቶችን (National Sex Offenders Registration System) መዘርጋት፣
- 3 የተሃድሶ መስጫ ማዕከላት ጥምረቶችን (Network) ማጠናከር፣
- 1,454 የፀረ ፆታዊ ጥቃት አስወጋጅ ግብረ-ሀይሎችን ማቋቋምና 9,010 ግብረ-ሀይሎችን ማጠናከር፣
- በሴቶች ህገ ወጥ ዝውውር ዙሪያ የ8,083,200 የህብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ በማሳደግ ህብረተሰቡ ችግሩን በመከላል ላይ ቀጥተኛ ተሳፊ እንዲሆን ማስቻል፣
- በተዘጋጀው Verification tool መሰረት 4,302 ቀበሌዎችን ከሴት ልጅ ግርዛት እንዲሁም 4,388 ቀበሌዎች ካለ ዕድሜ ጋብቻ ነፃ እንዲወጡ ማድረግ፣
- 63 የአንድ ማእከል አገልግሎቶችን በማቋቋምና ለ55 የአንድ ማዕከል /አንድ መስኮት/ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በማጠናከር 7,107 ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ሴቶችና ህፃናት ጥቃት ሲደርስባቸውና ለጥቃት ተጎጂ ከመሆናቸው በፊት የሚያሳውቁባቸው 14 የማሳወቂያ መስመሮች (Hotline service) አገልግሎቶችን ማቋቋም፣
- 10,219 ሴቶች የሆት ላይን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- 7 የሴቶች የተሃድሶ መስጫ ማዕከላትን በማቋቋም ጥቃት የደረሰባቸው 2,565 ሴቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤ እንዲሁም 611 የተሀድሶ አገልግሎት ላገኙ ሴቶች የስራ እድል መፍጠር፣

- በየደረጃው በሚገኙ 2,164,567 ሴቶች የኮቪድ- 19 ተጽእኖን ለመከላከል የሚያስችል የቁሳቁስ ድጋፍ ይደረጋል፣

## ግብ 2፡ የሴቶች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ

### ውጤት 1፡- ተሳትፎአቸው የተረጋገጠ ሴቶች፤

<u>የሚከናወኑ ተግባራት</u>

- ለሴቶች ተሳትፎ የህብረተሰቡን አወንታዊ አመለካከት በማሳደግ ዙሪያ ለ5,900,726 የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ይፈጠራል፣
- ለ9,076,507 ህብረተሰብ በሰላም ተሳትፎ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር ሴቶች በሰላም ግንባታና በግጭት አፈታት ያላቸውን ሚና ማሳደግ፣
- 6,967,366 ሴቶች በክረምትና በጋ መደበኛ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ፕሮግራም ላይ በመሳተፍ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ዘርፎች ላይ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ፣
- ለ1,125 የሚዲያ ባለሙያዎች በሴቶችና ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዙሪያ ስልጠና በመስጠት በሚዘጋጁ የሚድያ ፕሮግራሞች ላይ የሴቶች ጉዳይ በሚገባ እንዲሳልጥና የሚድያ ተቋማት በስርአተ ጾታ ጉዳይ ላይ ያቸውን ተሳትፎ ማሻሻል፣
- 460 የሴት አመራሮች ጥምረቶችን ማጠናከር፣
- የግንዛቤ ማስጨበጫ የንቅናቄ መድረኮችን በማካሄድ በሴቶች የአመራርና ውሳኔ ሰጪነት ዙሪያ የ777,796 ሴቶችን ግንዛቤ ማሳደግ፣

### ውጤት 2፡- ውክልናቸው የተረጋገጠ ሴቶች፤

<u>የሚከናወኑ ተግባራት</u>

- በአመራና ውሳኔ ሰጪነት ዙሪያ ለ 4828 ሴቶች ስልጠና በመስጠት ለአመራር በቁ የሆኑ የሴቶች አመራር ፑል መፍጠር፣
- በፌዴራል የሴቶች አመራርና ውሳኔ ሰጪነት ድርሻ በፌዴራል ካቢኔ 50%፣ በህግ አውጪ 30%፣ በህግ ተርጓሚ 30% ማድረስ፣

- በፌደራል ደረጃ ከአጠቃላይ የፓርላማ መቀመጫዎች በሴቶች የተያዙ መቀመጫዎች ድርሻን 38% ማድረስ፣
- በክልሎች የሴቶች አመራርና ውሳኔ ሰጪነት ድርሻ 35%፣ በህግ አስፈጻሚ 30%፣ በህግ አውጪ 30፣ በህግ ተርጓሚ 30%፣
- በክልል ደረጃ ከአጠቃላይ የምክር ቤት መቀመጫዎች በሴቶች የተያዙ መቀመጫዎችን ድርሻ 38% ማድረስ፣

## ግብ 3፡- የሴቶች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

## ውጤት 1፡- ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ሴቶች

<u>የሚከናወኑ ተግባራት</u>

- 3,791,364 ሴቶች በቁጠባ ላይ በመሳተፍ 2,098,554,584 ብር እንዲቆጥቡ ማድረግ፣ እንዲሁም ለ6,539,406 ሴቶች የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ 18,251,734,178 ብር በብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በጥቃቅንና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የሴቶች ባለቤትነት ድርሻ 50% ማድረስ፣
- ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት 498,005 ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እና በሕብረት ሥራ ማህበራት አባላት ውስጥ የሴቶች ድርሻ 40% እንዲደርስ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- ከሴቶች የስራ ክፍያ ጋር ተያይዞ ባሉ ችግሮችና መፍትሄዎች በሚመለከት 3 የዳሰሳ ጥናቶችና በማካሄድ ለቀጣይ እርምጃዎች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣
- ለ894,886 ሴቶች የገጠር መሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ ደብተር እንዲሰጣቸው ማድረግ፣
- ህብረተሰቡ ገንዘብ በማይከፈልባቸው የስራ መስኮች ዙሪያ ለ577,364 ሴቶች የግንዛቤ ማሳደግና 3 የዳሰሳ ጥናቶችን ማካሄድ፣
- በተስማሚ፣ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ የ1,331,762 የህረተሰብ ክፍሎችን ግንዛቤ በማሳደግ 1,549,692 ሴቶች እንዲሁም 15,517 የሴቶች ኢንተርፕራይዞች በተስማሚ፣ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በፌዴራልና በክልል 5 የሴቶች የገበያ ማእከላትን ማቋቋም፣

- 1 የሃምሳ (50) ሚሊዮን የአፍሪካ ሴቶች ፕሮጀክት ማሻሻልና ወደ ስራ ማስገባት፣
- በሃምሳ (50) ሚሊዮን የአፍሪካ ሴቶች ይናገሩ ፕሮጀክት ዙሪያ የ200 ሴቶችን ግንዛቤ ማሳደግ፣
- 2 በአገር አቀፍና በክልል የሴቶች ልማት ፈንድ ማቋቋም፣
- ለ727,333 ሴቶች በገቢ ማስገኛ መስኮች ላይ ስልጠና በመስጠት አቅማቸውን መገንባት እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ለ2,061,575 የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ማድረግ፣
- 22,893 የሴት ልማት ቡድኖችን በማቋቋምና 98,718 በማጠናከር እንዲሁም ወደ ላቀ ደረጃ ለደረሱ 1,143 የልማት ቡድኖች እውቅና በመስጠት በየደረጃው ሴቶችን የማጠናከር ስርአት ማጠናከር፣

**ውጤት 2፡- ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ሴቶች**

**<u>የሚከናወኑ ተግባራት</u>**

- 1 ሴቶች የርስበርስ ልምድ ልውውጥና ትስስር የሚያደርጉበት የሴቶች እኩልነት ማዕከል (Women's equality Hub) ማቋቋም፣
- ለ1,071 ሴት የመንግስት ሰራተኞች የትምህርት እድል በማመቻት የሴቶችን አቅም ማጎልበት፣
- 3,621 የአዳሪ ትምህርት ቤት ሴት ተማሪዎች የፋይናንስና የማቴሪያል ድጋፍ ማድግ፣
- በስነ ተዋልዶ ጤናና ኤች አይ ቪ /ኤድስ/ ዙሪያ 11,282,413 ግንዛቤ እንዲያኙ በማድረግ 2,672,272 ሴቶች የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ
- ለ 369,701 ሴቶች የህይወት ክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት 7,982,780 ሴቶች በተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- Mentorship Program ለ3,800 ሴት ተማሪዎች ትስስር መፍጠር እንዲሁም 152,770 ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለገቡ ሴት ተማሪዎች በMentorship Program ላይ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ፣
- የማህጸን መውጣት፣ ጡት ካንሰር፣ ፌስቱላ እና የማህፀን ጫፍ ካንሰር ቅድመ ምርመራ እንዲያደርጉ ለ9,405,332 ግንዛቤ መፍጠር፣

- የማህጸን መውጣት፣ ጡት ካንሰር፣ ፌስቱላ እና የማህፀን ጫፍ ካንሰር ችግር ላጋጠማቸው 5,271 ሴቶች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማመቻት፣
- በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ የ5,532,549 ግንዛቤ በማሳደግ ሴቶች በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ እና በአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራሞች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ፣
- 8,680 የሴት ተማሪዎች ክበባትን በማጠናከር ሴት ተማሪዎች በተለያዩ አካላት የሚደርሱባቸውን ተጽእኖዎች መቀነስ የሚያስችል አቅም እንዲያጎለብቱ ማስቻል፣

## ግብ 4፡ የሴቶች ተቋማዊነትና የተጠያቂነት ስርዓት ማጎልበት

**ውጤት 1፡- የሴቶች ማካተትና ተቋማዊነት፣**

<u>**የሚከናወኑ ተግባራት**</u>

- በስርዓተ ጾታ ማካተትና ተያያዥ ርዕሶች እንዲሁም በሀገራችን ቃል በገባችባቸው ሴቶችን የተመለከቱ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶችና የህግ ማህቀፎች ዙሪያ 233,625 ህረተሰብ ሙያዊ ድጋፍና ስልጠና መስጠት፣
- ለ1,361 ባለሙያዎች በስርዓተ ጾታ ማካተትና ተያያዥ ርዕሶች ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣
- 62 ተቋማት የሴቶችን ጉዳይ በፌደራልና በክልሎች ተቋማዊ እንዲያርጉ እንዲሁም 93 ተቋማት በፌደራልና በክልሎች እንዲያካትቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- የስርዓተ ጾታ ኦዲት ለማከናወን 14 ተቋማት ድጋፍ ማድረግ፤
- በየደረጃው የሚገኙ 127,265 ባለድርሻና አጋር አካላት አመራሮችና ባለሙያዎች የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና መስጠት፣

**ዉጤት 2፡- የተዘረጋና የተጠናከረ የአሰራር ስርዓት/የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም፤**

<u>**የሚከናወኑ ተግባራት**</u>

- አገር አቀፍ የሴቶች ፖሊሲን በመከለስ የሴቶችን መብት፣ ደህንነት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣
- በአወንታዊ ድጋፍ ርምጃ ተግባራዊነት ዙሪያ 1 ጥናት ማካሄድ፤

- 4 የትብብርና ቅንጅት ፎረሞችን በማጠናከር በተቀናጀ አሰራር የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ማሻሻል፣ ደህንነታቸውን ማስጠበቅና ፍትሀዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣
- 3 የስርዓተ ፆታ የመረጃ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ፤
- የስርዓተ-ጾታ ተቋማዊነት ለማረጋገጥ የተጀመረውን የስርዓተ-ጾታ የመረጃ ቋት (National Gender information System) ማጠናቀቅ፣
- 1 የስርዓተ ፆታ የመረጃ ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ለህብረተሰቡ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ተአማኒ መረጃ መስጠት፣
- ለ38 ተቋማት ድጋፍ በማድረግ የስርዓተ-ጾታ ማካተቻ፣ አናሊሲስ፣ ኦዲትና በጀቲንግ ማንዋሎችን እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣
- በስርዓተ ጾታ ማካተትና ተቋማዊነት ዙሪያ 15 የአሰራር ማዕቀፎችንና ሰነዶችን ማዘጋጀት፣
- የስርዓተ-ጾታ ማካተት ተቋማዊነትን ለማረጋገጥ 7 የተጠያቂነት አሰራር ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፣
- 7 የልምድ ልውውጥ በማካሄድ የሴክተሩን ስራ ማጠናከር፣
- በሴቶች ሴክተር ለሁሉም ተግባራት 19 ድጋፍና ክትትል ማከናወን ናቸው፡፡

## II. የህጻናት ዘርፍ

**ግብ 1፡- የህፃናት መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማረጋገጥ፤**

**ዉጤት 1፡- የተረጋገጠ የሕጻናት መብት**

<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት</u>

- የህጻናትን የልደት ሰርተፊኬት ተደራሽነት ለማሳደግ ከኢሚግሬሽንና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት እና የመረጃ የማሰብሰብ ስራን በማጠናከር 870,389 ህፃናት እንዲመዘገቡና የልደት ሰርተፊኬት ምዝገባ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡
- በህግ አባትነትን የማወቅ መብትን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት 1,013 የሚሆኑ ህፃናት በህግ አባትነትን የማወቅ መብት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

- ሚድያንና ሌሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎችን በመጠቀም በህፃናት መብትና ጥበቃ (ጥቃት፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ህገ ወጥ ዝውውር፣ ብዝበዛ፣ የህፃናት ስብእና ግንባታና ወዘተ…) በየደረጃው 7,185,918 ህብረተሰብ ግንዛቤ እንዲያገኝ የሚደረግ ይሆናል፡፡

**ዉጤት 2፡- የተረጋገጠ የሕጻናት ደህንነት፤**

<u>**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**</u>

- ለ2,778 የሴክተሩ፣ ለ3,701 የባለድርሻና አጋር አካላት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እንዲሁም ለ4,300,510 በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር የሚገኙ ህብረተሰብ በህጻናት መብትና ደህንነት ዙሪያ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና ይሰጣል፡፡

- የተሃድሶ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በማቋቋም እና በማጠናከር እንዲሁም የህጻናት ማህበራዊ አገልግሎት ስርዓትና የኬዝ ማኔጅመንት አሰራር በማጠናከር ከቤተሰብ ተለይተው በችግር ውስጥ በጎዳና ላይ ያሉ እንዲሁም ከስደት ተመላሽ የሆኑ 15,559 ህፃናት የማዋሃድና የማቀላቀል ስራ ይሰራል፡፡

- ከፌደራል ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ የክልል/ከተማ አስተዳደር ቢሮች እንዲሁም ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመተባበር ከዚህ በፊት የተቋቋሙ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶችን በማጠናከር በበጀት ዓመቱ *2,492* የሚሆኑ ጥቃት የደረሰባቸው ህጻናት በአንድ ማዕከል አገልግሎት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡

- 8 የተሃድሶ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በማቋቋም 6,528 ጥቃት የደረሰባቸው ህጻናት በማእከላቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባማድረግ የሕጻናትን ማህበራዊ ደህንነት የማሳግ ስራ ይሰራል፡፡

- ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ህጻናት ጥቃት ሲደርስባቸውና ለጥቃት ተጎጂ ከመሆናቸው በፊት የሚያሳውቁበት የማሳወቂያ መስመሮች (Hotline service) አገልግሎቶች በማመቻቸት 5,827 ህጻናትን በአገልገሎቱ ተደራሽ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

- በፍትህ ስርዓት የሚያልፉ ህፃናት ማለትም ጥቃት የደረሰባቸውና ጉዳይ በህግ የሚታይላቸው፣ ለምስክርነት የሚሄዱ፣ ህግን የተላለፉ እና ከወላጆቻቸው ጋር ወደ

ማረሚያ ቤት አብረው የሚገቡ ህፃናትን የሚያካተት ሆኖ ለሁለንተናዊ ጠቀሜታቸው ሲባል ጉዳዮች ለህጻናት ምቹ በሆኑ ችሎቶች የሚታይ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በ2014 በጀት ዓመት 240 ከዚህ በፊት የተቋቋሙ የህፃናት ተስማሚ ችሎቶችን በማጠናከር 2,468 ህፃናትን በምቹ የህፃናት ችሎቶች አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

- 4,805 ከዚህ በፊት የተቋቋሙና ስራ ላይ ያሉ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶችን ይበልጥ እንዲጠናከሩ በማድረግ እና 904 የሚሆኑ አዳዲስ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶችን በማቋቋም የህፃናት ድጋፍና ክብካቤ ፕሮግራሞች እንዲጎለብቱ የማድረግ ስራ በመስራት ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ይሰራል፡፡

- የህጻናትን መብት ከማስጠቅ አንጻር 6,495 የሚሆኑ የህጻናት መብት ግብረ ሃይሎች/ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡
- የህጻናትን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ከትምህርት ሚኒስቴር እና ሌሎች የፌደራል ተቋማት ጋር በመተባባር አካል ጉዳተኛ የሆኑ ህፃናት፣ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ህፃናት እንዲሁም በተግዳሮቶች ውስጥ የሚያልፉና ልዩ ድጋፍ የሚሹ በድምሩ *11,790* ህፃናት የተለያዩ አካላትን በማስተባበር እንዲደገፉ ይደረጋል፡፡
- ህግን ተላልፈው ለሚገኙ ህጻናትን ስብዕናቸውን ከመገንባት አንጻር በበጀት ዓመቱ 10 የሚሆኑ ህግን ተላልፈው የሚገኙ ህጻናት የተሃድሶ አገልግሎቶችን በማቋቋም 350 ህጻናት ስብዕናቸው እንዲገነባ እና ማህበራዊ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡
- የተቋቋሙ የአንድ ማዕከል አገልግሎቶችን በማጠናከርና 63 አዳዲስ ማእከላትን በማቋቋም 2,492 ጥቃት የደረሰባቸው ህጻናት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል፡፡

- 240 የህፃናት ተስማሚ ችሎቶችን በማጠናከር 2,468 ህፃናትን በምቹ የህፃናት ችሎቶች አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

- 4,805 ስራ ላይ ያሉ የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቶችን እንዲጠናከሩ በማድረግ እና 904 አዳዲስ ጥምረቶችን በማቋቋም የህፃናት ድጋፍና ክብካቤ ፕሮግራሞች እንዲጎለብት የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

- ❖ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ከትምህርት ሚኒስቴር እና ሌሎች የሚመለከታቸው የፌደራል ተቋማት ጋር በመተባባር አካል ጉዳተኛ ለሆኑና ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው 11,790 ህፃናት ድጋፍ ይደረጋል፡፡

- ❖ 6,495 የህጻናት መብት ማስጠበቅ ግብረ-ሃይሎች/ኮሚቴዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡

**ግብ 2፡ የህጻናትን ተሳትፎ ማረጋገጥ፣**

**ውጤት 1፡ የተረጋገጠ የህጻናት ተሳትፎ፣**

**<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤</u>**

- ❖ በየደረጃው 2,100 የሕጻናት ፓርላማዎችን በማቋቋም እና 10,778 ፓርላማዎች በማጠናከር 17,281 ህጻናት በህዝብ ምክር ቤቶች እንዲሳተፉ እና 1,193,160 የሚሆኑ ህጻናት በህጻናት ፓርላማ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

- ❖ በሀገር አቀፍ ደረጃ 1 የህፃናት ፓርላማ ማቋቋም፣
- ❖ በሚካሄዱ ኩነቶች (ዓለም አቀፍ የህፃናት ቀን፣ የአፍሪካ ህፃና ቀን፣ ልዩ የፈጠራ ክህሎት ያላቸው ህፃናት ፌስቲቫልና የFGM & Child Marriage Zero Tolerance Day) 5,028,724 ህፃናትና የህብረሰተብ ክፍሎች እንዲሳተፉ በማድረግ ህፃናት ድምጻቸው የሚያሰሙበት እንዲሁም ህብረተሰቡ በህፃናት ጉዳይ የሚወያይበት እድል ይፈጠራል፡፡

**ግብ 3፡- የህጻናትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣**

**ዉጤት 1፡- የተረጋገጠ የሕጻናት ማህበራዊ ተጠቃሚነት**

**<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት</u>**

- ❖ ህጻናት የተሻለ አስተዳደግ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከሚመለከታቸው የፌደራል ሴክተር መስሪያ ቤቶች እና የክልል/ከተማ አስተዳደር ቢሮዎች ጋር በመተባበር የህፃናት አያያዝና አስተዳደግ በሚል ፕሮግራም *3,924* ለሚሆኑ የቅድመ መደበኛ መምህራን እና *135,520* የህጻናት ቤተሰቦች ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
- ❖ የህፃናትን ሁለንተናዊ ስብዕና ለመገንባት 36 ምቹ የህፃናት መጫወቻና መዝናኛ ስፍራዎች እና የህፃናት ስብዕና ማዕከላት ለማስፋፋትና በልማት ግንባታዎች የህፃናትን

ምቹ መዝናኛና መጫወቻ ስፍራዎች በመገንባት 137,700 ህፃናት ተጠቃሚ ይደረጋሉ፡ ፡

- ❖ በመንግሰት ተቋማትና በማህበረሰብ ደረጃ 81 የህፃናት ማቆያዎች (day cares) በማቋቋም *7,078* ህፃናትን ተጠቃሚ ለማድረግ ይሰራል፡፡
- ❖ ህጻናት በተለያዩ አማራጮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር አንዱ በተቋማት ውስጥ ገብተው እንዲያድጉ በማድረግ ማህበራዊ ደህንነታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን በዚህ መሰረት በበጀት ዓመቱ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል ተቋማት ጋር በመተባበር *8,026* የሚሆኑ ህጻናት ወደ ተቋማት ገብተው እንዲያድጉና ማህበራዊ ደህንነታቸው እንዲረጋገጥ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በማህበረሰብ አቀፍ የህፃናት ድጋፍና ክብካቤ *1,070,343*፣ በተቋማት የ% ስፖንሰርሺፕ ድጋፍ *156,861* ህፃናት፣ በፎስተር ኬር *3,065* ህፃናት እንዲሁም በጉዲፈቻ *1,539* ህፃናት በድምሩ *1,239,834* ህጻናትን በመደገፍ ማህበራዊ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ የሚሰራ ይሆናል፡፡
- ❖ ህጻናት ለራሳቸው አወንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ለማስቻል እንዲሁም በመብታቸው እና ደህንነታቸው ዙሪያ በሚካሄዱ ፕሮግራሞች ተሳታፊ እንዲሆኑ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ *830,800* ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የሚፈጠር ሲሆን በተጨማሪም ህጻናት የሃገር ፍቅር እንዲኖራቸው እና በሀገራዊ አንድነት ዙሪያ *35,000* የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው ደደረጋል፡፡
- ❖ ህጻናት በራስ መተማመናቸውን ለመጨመር ራሳቸውን ከተለያዩ ጥቃቶች ለመከላከል እንዲችሉ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ 3,126 ህጻናት የህይወት ክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
- ❖ ህጻናት ከቤተሰቦቻቸው/ከማህበረሰቡ ጋር ጤናማ ግንኙነትና ጥብቅ ትስስር እንዲኖራቸው ለማድረግ *320,000* ለሚሆኑ ህጻናት ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው ይደረጋል፡፡
- ❖ የህጻናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ እና ደህንነታቸውን ከማስጠቅ አንጻር ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት *29,709* ለሚሆኑ የህጻናት ቤተሰቦች የማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ እንዲገኙ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡
- ❖ የህጻናትና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ አንጻር ወላጆች/ ቤተሰቦች ህፃናትን በጉዲፈቻ፣ በአደራ ቤተሰብ እና በስፖንሰርሺፕ ድጋፍ እንዲሳተፉ የሚያስችል ስልጠና

በመስጠት ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በበጀት ዓመቱ *11,738* ቤተሰቦች ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ድጋፍ እንዲያደርጉ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

- ❖ የህጻናት አስተዳደግ (ስብዕና) ለመገንባት በክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች በየደረጃው በተቋቋሙ የስብዕና ማዕከላት 937,700 ህጻናትን ተጠቃሚነእንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

- ❖ የሕፃናትን መብትና ደህንነትን ለማስከበር በተዘጋጁ ዋና ዋና የአሰራር ማእቀፎች እና ሌሎች ተግባራት ዙሪያ *2,957* ለሚሆኑ የፖሊስ አባላት በህፃናት መብትና የህፃናት ጥበቃ የኬዝ ማኔጅመንት ስርዓት አቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በቀበሌ ደረጃ *1,243* በጎ ፈቃደኛ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች በህፃናት የህፃናት ጥበቃ ዙሪያ በማሰማራት የህጻናትን ማህበራዊ ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

- ❖ ህፃናት የሚቆዩባቸው አማራጮች ባለመኖራቸው ምክንያት ከወላጆቻቸው ጋር ወደ ማረሚያ ቤት የሚገቡ ህፃናት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሆኑ በ2014 በጀት ዓመት *431* ያለጥፋታቸው በማረሚያ ቤቶች ከወላጆቻቸው ጋር የሚገኙ ህፃናት በሌሎች አማራጮች የሚደገፉበትን ሁኔታ የሚመቻች ይሆናል፡፡

- ❖ በበጀት ዓመቱ 12 የአሰራር ማእቀፎችን በማዘጋጀት የህጻናትን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚሰራ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የህጻናትን ማህበራዊ ደህንነት አስመልክቶ 4 ሃገራዊ ጥናት ይደረጋል፡፡
- ❖ የህጻናትን መብት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት አስመልክቶ በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራትን አፈጻጸም ለመገምገምና ለመከታተል 13 የድጋፍና ክትትል ስራዎች የሚደረጉ ይሆናል፡፡

**III. በወጣቶች ዘርፍ**

**ግብ 1- የወጣቶች መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማረጋገጥ፤**

**ውጤት 1፡- መብታቸው የተረጋገጠ ወጣቶች፤**

<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤</u>

- ❖ 4,969,764 ወጣቶች በአዲስ በመደራጀት መብትና ጥቅማቸውን እንዲያስጠብቁ በማድረግ የተደራጁ ወጣቶችን ድርሻ ከ8.6 % ወደ 15% የማድረስ ስራ ይሰራል፣

- የወጣት አደረጃጀቶችን ያሉባቸውን ችግሮች በሚመለከት 1 አገር አቀፍ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣ በክልልና 2ቱ ከተማ አስተዳደሮች 14 የመንግስት ሰራተኞች የወጣቶች ፎረም እንዲቋቋም ማድረግ፣

- አገር አቀፍ የወጣቶች ካውንስል (ም/ቤት) ለመመስረት በተዘጋጀው የወጣቶች ካውንስል መመስረቻ ሰነድ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር በየደረጃው 12 የወጣት ካውንስሎችን በማቋቋም 1 አገር አቀፍ ካውንስል እንዲማቋቋም ይደረጋል፡፡

- **ለ152,980 ወጣት አደረጃጀት አመራሮችና አባላት የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት የመፈጸምና የማስፈጸም አቅማቸውን መገንባት፣**

- ለ1,715 የወጣት አደረጃጀቶች ተቋማዊ ብቃታቸውን ለመገንባት የሚያስችሉ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፎችን ማድረግ፣

- በፌዴራልና በክልሎች 10 የወጣት አደረጃቶችን ምርጥ ተሞክሮ ቀምሮ ማስፋት፣

- 4,969,764 ወጣቶችን በአዲስ እንዲደራጁ በማድረግ መብትና ጥቅማቸውን እንዲያስጠብቁ የማድረግ ስራ ይሰራል፣

- በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢ ለሚኖሩ 1,459,503 ወጣቶች በመብትና ደህንነታቸው ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል፣

**ዉጤት 2፡- ደህንነታቸው የተጠበቀ ወጣቶች፤**

**<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤</u>**

- ለ3,034,851 ህብረተሰብ በወጣቶች መብት፣ ደህንነትና ህገ ወጥ-ዝውውር ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ይሰራል፣

- ለ10,956 ልዩ ድጋፍ የሚሹና አካል ጉዳተኛ ወጣቶች መብት፣ ደህንነትና ተጠቃሚነትን አስመልክቶ ስልጠና በመስጠት አቅማቸውን ማሳደግ፣

- **ለ5,580,195** ለሚሆኑ ወጣቶች **የአየር ንብረት** ለውጥ የሚያስከትላቸውን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታና በአገራችን የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም ላይ በንቃትና በተደራጀ መልኩ እንዲሳተፉ ማድረግ፣

ግብ 2፡ የወጣቶች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ፣

ውጤት 1፡ ተሳትፎአቸው የተረጋገጠ ወጣቶች

<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤</u>

- ❖ 23,000,000 ሚሊዮን ወጣቶች በመደበኛ፣ 50 በድንበር ተሻጋሪ እና 130 በወሰን ተሻጋሪ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በመሰማራት በመንግስትና በማህበረሰቡ ያልተሸፈኑ የልማት ስራዎችን በመስራት 48.50 ሚልዮን ማህበረሰብ በአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ 10 ቢሊዮን ብር ሀብት የማዳን ስራ ይሰራል፡፡
- ❖ 3,142,626 ሚሊዬን ህብረተሰብ ክፍሎችንን በመደበኛ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማሰማራት ስራ ይሰራል፣
- ❖ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሰማርተው የላቀ አፈጻጸም ላሳዩ ለ177,591 ለሚሆኑ ወጣቶች እውቅናና የማበረታቻ ሽልማት በመስጠት ወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ባህል እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- ❖ በየደረጃው የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በሚመለከት 17 ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ በማስፋት በየደረጃው ወጣቶች በበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማሻሻል፣
- ❖ ብሔራዊ የወጣቶች በጎ ፈቃድ ፖሊሲ ማጠናቀቅና ማሰራጨት እንዲሁም የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድን ማሻሻል፣
- ❖ በሁሉም ክልሎችና 2ቱ ከተማ አስተዳሮች በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ኮቪድ-19ን በመከላከል ያበረከቱትን አስተዋፆ የሚያሳይ 10 ዘጋቢ ፊልሞችን ማዘጋጀት፣
- ❖ በኮቪድ- 19 መከላከል ዙሪያ የግንዛቤና ንቅናቄ ፕሮግራሞችን በማካሄድ የ2,248,250 ህብረተሰብ ግዛቤ ማሳግ፣ ለ1,568,370 ህረተሰብ የኮቪድ-19 ተጽእኖን መከላከል የሚያስችል የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፡፡
- ❖ በየደረጃው የግንዛቤና ንቅናቄ ተግባራትን በማከናወን 10,708,728 ወጣቶች በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

**ውጤት 2፡ ውክልናቸው የተረጋገጠ ወጣቶች**

**<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤</u>**

- ❖ በተካሄደው 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ወጣቶች በአመራርና ውሳኔ ሰጪነት የወጣቶችን ድርሻ በህግ አውጪው 32% በህግ አስፈፃሚ 38%፣ በህግ ተርጓሚ 25% ማድረስ በጥናት ይለያል፡፡

**ግብ 3፡- የ ወጣቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ**

**ውጤት 1፡- ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጡ ወጣቶች፤**

**<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤</u>**

- ❖ ከህብረት ስራ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር 184,747 ወጣቶች በህብረት ስራ ማህበራት እንዲደራጁ፣ 6,209,589 ወጣቶች በቁጠባ ላይ በመሳተፍ 5.275 ቢሊዮን ብር እንዲቆጥቡ ማድረግ እና 1,283,845 ወጣቶች የ9.1 ቢሊዮን ብር ብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማሻሻል ስራዎች እንዲከናወኑ ይሰራል፣
- ❖ 706,822 የሚሆኑ ወጣቶችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፣
- ❖ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለ201,357 ወጣቶች የገበያ ትስስር እንዲመቻችላቸው፣ 225,887 የማምረቻና 6,105 ለሚሆኑት ወጣቶች የመሸጫ ቦታ አቅርቦት እንዲመቻችላቸው ማስተባበርና መከታል፣
- ❖ በተስማሚና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር 807,850 ወጣቶች ተጠቃሚ ማድረግ፣
- ❖ የትብብርና ቅንጅት ስራዎችን በማጠናከር አገር አቀፍ የስራ ፈላጊ ወጣቶች የመረጃ ቋት ማደራጀት፤ ለ2,956,780 ሚሊዮን ወጣቶች የስራ እድል እንዲፈጠር 4 የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን ማከናወን፣
- ❖ የኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም በስራ ፈጠራ (ኢንተርፕሩነርሺፕ) እና በስራ ባህል መዳበር ዙሪያ ለ3,100,281 ወጣቶች የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና በመስጠት ለ80 ባለተሰጥዖ ወጣቶች እውቅና መስጠት፣

- የወጣቶች የልማት ፈንድ እንዲቋቋም የሚያስችል መመሪያ ማዘጋጀት፣ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በወጣቶች ላይ ያስከተለውን ተፅዕኖ ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ማሄድ፣ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑና ከስደት ተመላሽ ወጣቶች ዙሪያ 2 የክትትልና ድጋፍ ፕሮግራሞችን በማካሄድ የተጠናከረ መረጃ የማደራጀት ስራ መስራት፣
- በወጣቶች ተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ አፈጻጸምና በኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በተመለከተ 35 የውይይት መድረኮችን ማካሄድ፡፡

**ውጤት 2፡- ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ወጣቶች**

<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤</u>

- በከፍተኛና በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ወጣቶች ከአምራች ድርጅቶችና ኢንዱስትሪዎች ጋር የተግባር ልምምድ/Internship and Apprenticiship/ የሚያደርጉበት የአሰራር ሰርአት መዘርጋት፣
- የወጣት ስብዕና ልማት ማዕከላትና የጤና ተቋማት ወጣት ተኮር ጤና አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የሚያስችል የአሰራር ስርዓቶች እንዲዘረጋ በማድረግ 2,168,956 ወጣቶች የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
- አሉታዊ መጤ ልማዶች፣ አደንዛዥ ዕፆች፣ የስፖርት ውርርድ እና ሱሰኝነት በወጣቶች ላይ የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ አስመልክቶ 5 ዘጋቢ ፊልሞችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣
- በፌዴራልና በክልሎች የሚገኙ 13 የአሉታዊ መጤ ልማዶችንና አደንዛዥ እጽ የመከላከል ግብረ-ሃይሎች ያከናወኗቸውን ተግባራት መከታተልና መደገፍ፣
- በሁሉም ክልሎችና 2ቱ ከተማ አስተዳደሮች 535 አዳዲስ የወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከላትን በመገንባት፣ 698 ማእከላትን በማጠናከርና 933 ማእከላት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ በማድረግ 10,795,466 (2,736 አካል ጉዳተኛ ወጣቶች) በማዕከላቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የወጣት ማዕከላትን ወደ ሶሻል ኢንተርፕራይዝ ለማሳደግ 1 ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት፣

- በወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከላት ችግሮች ዙሪያ በየደረጃው ካሉ አመራሮችና ባለሃብቶች ጋር የውይይት መድረክ በማካሄድ በ16 ማእከላት የሶሻል ኢንተርፕራይዝ ፕሮግራም ተግባዊ ማድረግ፤

- በትምህርት ተቋማት የወጣቶችና የህፃናት የስብዕና ግንባታ ክበባትን ለማቋቋም በ12 ትምህርት ተቋማት ንቅናቄ መፍጠር፣
- ሞዴል የአፍሪካ ወጣቶች የትስስር ማዕከልን በአዲስ አበባ ከተማ ለመገንባት የፕሮጀክት ሰነድና የግንባታ ዲዛይና በማዘጋጀት ሀብት ማሰባሰብ፣

- በሁሉም ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለሚማሩ 420,140 ወጣቶች እንዲሁም በተመረጡ ማረሚያ ቤቶች የዕርምት ጊዜያቸውን በማጠናቀቅ ላይ ለሚገኙ 3,776 ታራሚ ወጣቶች በስብዕና ልማትና በአስተሳሰብ ለውጥ /Mind Set/ ዙሪያ እንዲሁም ለ4,951,277 ወጣቶች የህይወት ክሎት ስልጠና በመስጠት አዎንታዊ አስተሳሰብን እንዲያዳብሩ ማስቻል ተግባር ይከናወናል፣

- የሚዲያና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የወጣቶችንና የታዳጊ ወጣቶችን ስብዕና በመገንባት ረገድ አዎንታዊ ሚናቸውን እንዲወጡ የሚያስችል 16 የምክክር መድረክ ማሄድ፣

- ስብዕናው የጎለበተ ትውልድ በመቅረፅ ረገድ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት 29 ውይይት መድረኮችን በማካሄድ፣

- የማህበረሰብ አቀፍ ሬዲዮ ጣቢያዎች በታዳጊ ወጣቶች ስብዕና ግንባታ ዙሪያ እንዲሰሩ የአሰራር ስርዓት የመዘርጋት ስራ ይሰራል፡፡

- ለ2,100 ለሚሆኑ ወጣቶች የሀገራችን ወጣቶች እርስ በርዕስ የሚገናኙበት የዩዝ ኮኔክት ኢትዮጵያ ፕሮግራምን ማስተዋወቅ 3 የቪዲዮ ኮንፈረንስ /hangout/ መድረክ ማካሄድ፤

- ከመንግስት ከፍተኛ አመራሮች ጋር 5 አገር አቀፍ እና ክልላዊ የወጣቶች ኮንፈረንስ በማካሄድ በመንግስትና በወጣቶች መካከል አዎንታዊ ግንኙነትን ማጠናከር፡፡

- በወጣቶች ጥያቄዎችና ወቅታዊ ችግሮች ዙሪያ 12 የመወያያ ሠነዶችን በማዘጋጀት ግንዛቤ መፍጠር፤ 6 መድረኮችን በማካሄድ የወጣቶች ስብዕና ግንባታ የአተገባበር

መመሪያ፣ የወጣት ማዕከላት የዘላቂነት ስትራቴጂ የወጣት አገር አቀፍ ማዕከላት የዳሰሳ ጥናት ማስተዋወቅና አሳትሞ ማሰራጨት፣

- በወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከላት ችግሮች ዙሪያ በየደረጃው ካሉ አመራሮችና ባለሃብቶች ጋር 33 የውይይት መድረኮችን በማካሄድ ችግሮቹን መፍታት የሚያስችል ቅንጅታዊ የአሰራር ስርአት መርጋት፣
- ለ281,330 ወጣቶችን በሚመለከቱ አለማቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች፣ የድርጊት መርሀ-ግብሮችና ቻርተሮች (አጀንዳ 2030፣ አጀንዳ፣ አጀንዳ 2063 ፣ 2250፣ የአፍሪካ የወጣቶች ቻርተር) ማስተዋወቅና ግንዛቤ መፍጠር፣
- በኩነቶችን (የዓለም ወጣቶች ቀን፣ የአፍሪካ የወጣቶች ቀን፣ የዓለም በጎ ፈቃደኞች ቀን ምክንያት በማድረግ) ለ644,768 የህብረተሰብ ክፍሎችና 7,219,916 ወጣቶች በአዎንታዊ የወጣች ልማት ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር፣
- 624 ለሚሆኑ የሚዲያና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ወጣት ተኮር ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትና በመዘገብ ረገድ አወንታዊ ሚናቸውን እንዲወጡ በማስቻል ለ1,227,056 ህብረተሰብ በወጣቶች ሁለንተናዊ ልማት ላይ እንዲሳተፍ ግንዛቤ መፍጠር፣

**ግብ 4፡- የተቋማትን ተቋማዊ ብቃት ማሳደግ**

**ውጤት 1፡- የጎለበተ የመፈፀምና ማስፈጸም አቅም**

<u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፤</u>

- 19 የክትትልና ግምገማ ፕሮግራሞችን በማካሄድ በፌዴራልና በክልል የሚገኙ ሴክተሮች ከተግባርና ኃላፊነታቸው አኳያ በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮጀክቶች፣ ፕሮግራሞችና የልማት እቅዶች የወጣቶችን ጉዳይ ማካተታቸውን ማረጋገጥ፣
- በወጣቶች ጉዳይ ማካተት ዙሪያ በፌዴራል በክልሎች 8 የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፎረሞችን ማቋቋም፣

- 192 ተቋማት የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ ማድረግ እንዲሁም 32 የፌዴራልና የክል ተቋማት የወጣቶችን ጉዳይ ተቋማዊ እንዲያደርጉ ማስቻል፣

- ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ የአፈፃፀም ጥናት በማካሄድ የፖሊሲ ክለሳ ምክረ-ሀሳብ ማቅረብ፤

- በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ 8,901 ኃላፊዎች፣ ባለድርሻና አጋር አካላት አመራሮችና ባለሙያዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ስልጠና በመስጠት የመፈጸምና የማስፈጸም አቅማቸውን በመገንባት ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት ተግባራት፣

- በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር እንዲሁም ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ለሚገኙ 1,459,503 ወጣቶች በመብቶቻቸው፣ ደህንነታቸውና ግዴታዎቻቸው ዙሪያ ስልጠና መስጠት፣

- በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር እንዲሁም ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች 12 የድጋፍና ክትትል ፕሮግራሞችን ማካሄድና ክፍተቶቻቸውን በመለየት የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣

- 6,038 የወጣቶች ወላጅ ፎረም መመስረት፣

- 1 ብሔራዊ የወጣቶች ረቂቅ ፖሊሲ ጥናት ማካሄድ፣
- አገር አቀፍ የወጣቶች መረጃ ቋት /Youth Management Information Sysytem/ ማቋቋም፣

- 1 የወጣቶች የመረጃ ቋት /Data base/ መገንባት፣

## IV. የማህበራዊ ጥበቃ ዘርፍ፤

## ግብ 1. የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፤

**ውጤት 1፡ የተደራጁና ወደ ሥራ የገቡ ምክር ቤቶች፣**

<u>የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ብሄራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርዓት /MIS/ ለማስተግበና ለመምራት ራሱን ችሎ የተቋቋመው የስራ ክፍል በሰው ኃይል በማሟላት ሥራ እንዲጀምር ማድረግ፣
- የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ተጠቃሚዎችን መረጃዎች ወጥነትና ተመጋጋቢነት ባለው መንገድ ከፌደራል እስከ ወረዳ አደራጅቶ ለመያዝ የሚያስችል የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ስርዓት በመዘርጋት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ፍትሃዊ ተደራሽነትን ማሳደግ፣
- የተቀናጀ የማህበራዊ ጥበቃ የመረጃ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል አንድ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስልጠናን ማስተዳደሪያ የሚሆን የኦቶሜሽን ሥራ መስራት፣
- ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረቡትን የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ እና የማህበራዊ ጥበቃ ካውንስል ማቋቋሚያ አዋጆች እንዲጸድቁ መከታታል፣ የማስፈጸሚያ ደንቦችና መመሪያዎችን በማጸደቅ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ እና ክልላዊ የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤቶችን እና የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ ምክር ቤቶችን ለሚያቋቁሙ ክልሎች ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣
- የማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ችግሮችን በመከለከልና የችግሩ ሰላባ የሆኑትን በማቋቋም ቤተሰብ ተገቢ ሚናውን የሚወጣበት አንድ የአደረጃጀትና የአሠራር የህግ ማዕቅፍ በማዘጋጀት ጸድቆ ስራ ላይ እንዲውል ለሚመለከተው የውሳኔ ሰጭ አካል ማቅረብ፣
- የማህበራዊ ጥበቃን የመፈፀም አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ 10 (አስር) ሰነዶችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ ( Contract Management Manual፣ Communication Strategy and Plan, Child to Family Reunification/Reintegration Operational Guideline, Safeguarding and Grievance Redress Mechanism GRM, Educational Services Guideline, Guideline for Health Services for the Homeless UD, Service Standard for Organizations Providing Services to Homeless Elder, Adult and Women with Children peoples, Networking guideline for urban destitute service providers, Comprehensive Social Protection programs Monitering &Evaluation Tools).
- 75507 የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን የሚያስተባብሩ የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤቶችን (ካውንስሎችን) በማቋቋም የማህበራዊ ጥበቃ ተደራሽነትንና ሽፋኑን ማሳደግ፣

**ግብ 2. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ቤተሰቦችን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ እና ኑሮ ሁኔታ በማሻሻል ከድህነት እንዲወጡ ማድረግ፣**

**ውጤት 1፡ ማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ተጠቃሚነታቸው የጨመረ በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት የታቀፉ ድሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፤**

<u>የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

- በገጠርና በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም/ፕሮጀክት በታቀፉ ወረዳዎችና ከተሞች የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች ወቅቱን የጠበቀ ወርሀዊ ክፍያ እየተላለፈላቸው መሆኑን በየሩብ ዓመቱ በመስክ ምልከታና በክትትል በማረጋገጥ ስለአፈፃፀሙም ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ መልስ መስጠትና ሪፖርት ማቅረብ፣
- በአንደኛው ዙር የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት በታቀፉ 11 ከተሞች የሚገኙ የጎዳና ተዳዳሪዎችን ለማቋቋም ውል የገቡ 76 የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በገቡት ውል መሰረት አገልግሎቱን እየሰጡ ስለመሆናቸው በየሩብ ዓመቱ የመስክ ምልከታ በማድረግ መደገፍ፣ መከታተል እና ስለአፈፃፀማቸውም ግብረ- መልሰ መሰጠት፣
- የገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም እና የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት የቀጥታ ድጋፍ እና የኑሮ ማሻሻያ የኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ፕሮጀከት ተግባራዊ አፈጻጸምን ለማሳደግ የሚያስችል በየሩብ ዓመቱ የመሰክ ምልከታ በማድረግ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ማካሄድ (መደገፍ፣ መከታተል፣ መገምገም እና መቆጣጠር)፣ ስለአፈፃፀሙም ለፈፃሚዎችና ለሚመለከታቸው አካላት ግብረ-መልሰ መሰጠት፣
- የከተማ እና የገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት/ፕሮግራምን/ አፈጻጸም ለማሳደግ ከፈጻሚ ተቋማት እና ከልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ በሚካሄደው የተቀናጀ የአፈፃፀም ድጋፍና ክትትል (JRIS) መድረክ ላይ በመሳተፍ የፕሮግራሙን/የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ማጎልበት፣
- በአንደኛውና በሁለተኛው ዙር የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክቶት በታቀፉ 22 ከተሞች የሚገኙ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎችን ከጎዳና ላይ በማንሳት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን በማስተወቂያ በመጋበዝ እና በመለየት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣

- የገጠርና ከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም/ፕሮጀክት አፈጻጸምን ለማጎልበት የሚያስችል ስልጠና ለፈጻሚና ለስራው ባለድርሻ ተቋማት የሚሳተፉበት (የአፈጻጸምና የልምድ ልውውጥ የሚካሄድባቸው) ሁለት መድረኮችን በማዘጋጀት ተፈፃሚ ማድረግ ፣
- በከተማና በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት የተቀናጀ የማህበራዊ ጥበቃ የመረጃ ሥርዓትን MIS ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል አራት የስልጠና መድረኮችን በማዘጋጀት በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መዋቅርና ለሚመለከታቸው ፈፃሚ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፣
- በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የማህበረሰብ ሥራ ተሳታፊዎች የሙያ ላይ ደህንነትና ጤንነት ላይ ሁለት ጊዜ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣

## ግብ 3፡ የኢኮኖሚያዊ እና የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፤

### ውጤት 1፡ የኢኮኖሚያዊ እና የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ይጨምራል፣

<u>የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

- በፌደራልና በክልል ያሉ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የብሄራዊ ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ አተገባበርን ውጤታማነትን በማሳደግ የበኩላቸውን ድርሻ ለመወጣት እንዲችሉ ሁለት መድረኮችን በማመቻቸት ስልጠናዎችን መስጠት፣
- የተቀናጀ የማህበራዊ ጥበቃ የመረጃ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል ሁለት የስልጠና መድረኮችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት የመረጃ ቴክኖሎጂ አያያዝና አስተዳደር ስልጠና መስጠት፣
- በፌደራል ደጃ ያለው የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት ተቋቁሞ ስራውን እስኪጀምር ድረስ አሁን በመተካት በጊዚያዊነት ተቋቁሞ (ብሄራዊ መህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲና ስትራቴጅ በመፈጸምና በማስፈፀም ቁልፍ ሚና ያላቸውን የመንግስትና የልማት አጋር ተቋማትን በማካተት) ሥራውን በመስራት ላይ የሚገኘውን የብሄራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፕላት ፎርም አመታዊ እቅድ ማዘጋጀት፣ ወህራዊ የስብሰባን መድረኮችን በማዘጋጀትና በመምራት አፈፃፀሞች እንዲገመገሙ በማድረግ ለየተቋማቱ ስለአፈፃፀማቸው ግብረ መለስ መስጠት፣

- በከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድግ የሚተገበረውን የፕሮጀክት አፈጻጸም ለማሳደግ የሚመለከታቸው የመንግስት አስፈጻሚ ተቋማት፣ የልማት አጋሮች እንዲሁም አገለግሎቱን በመስተዋ ላይ የሚገኙ ተቋማት የሚሳተፉበት ወህራዊ የምክክር እና የልምድ መለዋወጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ተፈጻሚ ማድግ ፣
- የማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረቶች (CCCs) አደረጃጀትና አስራርን ውጤታማነት ለማሳደግ የሚያግዝ አንድ መድረክ በማዘጋት ጉዳየ ከሚለከታቸው የፌደራልና የክልል ተቋማት ተቋማት ለተውጣጡ ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና መስጠት፣
- የተቀናጀ የማህበራዊ ጥበቃ የመረጃ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል ሁለት የስልጠና መድረኮችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት የመረጃ ቴክኖሎጂ አያያዝና አስተዳደር ስልጠና መስጠት፣
- የንግዱ ማህበረሰብ የማሕበራዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ለማስቻል አንድ መድረክ በማቻቸት በመ/ቤቱ የተዘጋጀውን የኮርፖሬት ሶሻል ሪስፖንሲብሊቲ የአሠራር ጋይድላይን ማስተዋወቅ፣
- በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ዙሪያ ለመስራት ፈቃድ ያገኙ ድርጅቶች በገቡት ውል መሠረት ተገቢ ሚናቸው ስለመወጣታቸው ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ስለአፈፃፀማቸው ግብረ-መልስ መስጠት፣
- ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር የአደገኛ ዕጽና መድሃኒቶች በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችል አንድ ወጥ አገራዊ እቅድ በማዘጋጀት ተፈጻሚ ማድረግ፣
- ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ውል የገቡት የኢትዮጵያ ሶሶሎጅስቶች፣ሶሻል ወርከሮች እና አንትሮፖሎጅስቶች ማህበር እና FHI 360 (Family Health International) ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ለማጎልበት የሚያስችል ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ስለአፈፃፀማቸው ግብረ-መልስ መስጠት፣
- በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ በሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ዙሪያ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለመስጠት ለሚፈልጉ ድርጅቶች/ ግለሰቦች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፣

- ሁሉም ክልሎችና የፌደራል ከተማ አስተዳደር የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መ/ቤቶች እያደገ የመጣውን የጎዳና ተዳዳሪነት ለመከላከልና የችግሩ ሰለባ የሆኑትን ለማቋቋም የሚያስችሉ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማስተባበር፣ መምራት እና አፈፃፀማቸውንም በየጊዜው በመገምገም ግብረ-መልስ መስጠት፣
- የገጠርና የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት የቋሚና ጊዜያዊ ቀጥታ ድጋፍ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ቤተሰቦችን ከመሠረታዊ ማህበራዊ አገልግሎቶች ጋር በማስተሳሰር ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል አገልግሎት ሰጭ ለሆኑ የፌደራልና የክልል ተቋማት አመራርና ባለሙያዎች አንድ መድረክ በማዘጋጀት የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና መስጠት፣
- ለከተማና ለገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች/ፕሮክጅት ማስፈጸሚያ የተዘጋጁ ሰነዶችን ተፈጻሚነት ለማሳደግ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው እና ለባለድርሻ አካላት ተቋማት ሃላፊዎች እና ባለሙያዎች በ6 መድረኮች ስልጠናዎችን መስጠት፣
- የከተማና የገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት የቀጥታ ድጋፍ ንዑስ ፕሮግራም አፈጻጸምን ለማሻሻልና ለማጎልበት እንዲቻል የሠ.ማ.ጉ ሴክተር ፈፃሚና አስፈጻሚ እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ሁለት የጋራ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ተፈጻሚ ማድረግ፣
- የክልልና የከተማ አስተዳደር ሠ.ማ.ጉ ሴክተሮች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት የገጠር እና ከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት የኑሮ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም የቅጥር ሥራ ዘርፍ በአግባቡ ተፈፃሚ ለማድረግ እንድችሉ በሁለት መድረኮችን በማዘጋጀት የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣
- የሰቆጣ ዲክላሬሽን እና የጊምቢቾ ወረዳ ትርንስፎርሚሽን ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት፣
- 9,338 የገጠርና ከተማ የቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎችን የቤት ለቤት ጉብኝት በማካሄድ የተሐድሶና ድጋፍ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ
- 103,768 በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች በከፋ ድህነት ውስጥ የሚገኙት አረጋዊያን የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሥነ-ልቦናና ማህበራዊ ተሀድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ
- 120,068 በክልል ዋና ዋና ከተሞች ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች (Urban destititute) የስነ ልቦናና ማህበራዊ ተሀድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ

- 58,572 ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በተለያዩ የሥራ መስኮች መሳተፍ ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ አረጋውያን የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የትምህርት፣ የስልጠና እና የሥራ ስምሪት ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳትፎአቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፣
- 5,329 ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በተለያዩ የሥራ መስኮች መሳተፍ የሚችሉ ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የትምህርት፣ የስልጠና እና የሥራ ስምሪት ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳትፎአቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፣
- 27,512 ማህረሰብን መሠረት አድርገው የተዋቀሩ አደረጃጀቶች፣ ሲቪክ ማህበራት እና የንግዱ ማህበረሰብ ለአረጋዊያን ዜጎች የድጋፍ እና የእንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ በማድረግ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣
- ማህረሰብን መሠረት አድርገው የተዋቀሩ አደረጃጀቶች፣ ሲቪክ ማህበራት እና የንግዱ ማህበረሰብ ውሎና አዳራቸው ጉዳና ላይ ላደረጉ ዜጎች የድጋፍ እና የእንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ በማድረግ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣
- 52084 ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ከድህነት ወለል በታች የሚገኙትና ዕድሜያቸው ከ70 ዓመት በላይ የሆኑ አረጋዊያን መካከል የአካል ድጋፍ አገልግሎትና የማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶች እንዲያገኙ በማድረግ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፣
- 5110 ተከታታይነት ያላቸው በየዓመቱ የሥልጠናና የግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮችን በመፍጠር የህብረተሰቡን የሚመለከታቸው አካላት የሚያድርጉትን ድጋፍና እንክብካቤ ማሳደግ፣
- 32716 የማኅበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን አቀናጅቶ እና አስተባብሮ ለመምራት የሚያስችል የማኅበራዊ ጥበቃ ምክር ቤቶችን ማቋቋም፣
- 6 አዲስ የአረጋዊያን ማህበራትን እንዲቋቋሙ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣
- 2271 ነባር የአረጋዊያን ማህበራት እንዲጠናከሩ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣
- ሴተኛ አዳሪዎች የምክር (Guidance) እና የምክክር (Counseling) አገልግሎት በመስጠት የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፣

- ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ ቀበሌዎች ላይ አዲስ የድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶችን (CCC) ማቋቋም፣
- 2,494 ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ ቀበሌዎች ላይ ነባር የድጋፍና እንክብካቤ ጥምረቶችን (CCC) ማጠናከር፣
- የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር 988 ሴተኛ አዳሪዎች በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ፣
- ለ151,600 የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠት እና በማቋቋም ችግሩን መቀነስ፣
- የኮሮና ቫይረስ ተፅዕኖ ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች መረጃ የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም መለየት፣
- በቫይረሱ የተጠቂ የሆኑ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን ድሀና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማረጋገት የሚያስችል ሳይኮሶሻል ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ውሎና አዳራቸው ጎዳና የሆኑ በቫይረሱ ስርጭት ጉዳት እንዳይደርስባቸው የተለያዩ ረጂ ድርጅቶችን በማስተባበር ወደ ሚረዱበት ማዕከላት ማስገባት፣ በዘላቂነትም የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

**ግብ 4፡ የአቅም ግንባታ፣ የግንዛቤ እና አድቮኬሲ ሥራዎችን በማስፋፋት የአረጋዊያንን ሁለንተናዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣**

**ውጤት 1፡ ተጠቃሚ የሆኑ አረጋዊያን፤**

<u>**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**</u>

- ዕቅድ እና የሥራ አፈጻጸምን መሰረት በማድረግ ለኢትዮጵያ አረጋዊያንና ጡረተኞች ብሔራዊ ማህበር ዓመታዊ የገንዘብ ድጎማ ድጋፍ በማድረግ የመፈጸም አቅማቸውን ማሳደግ፣
- በአረጋውያን ዙሪያ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ ከአንድ ክልል በላይ የሚሰሩ 15 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን አፈፃፀም በመገምገም ግበረ-መልስ መስጠት፣
- የአረጋዊያን ማህበራት አመራር አካላት እና አስፈጻሚዎችን አቅም የሚያጎለብት ስልጠና በመስጠት የማህበራቱን ሚና ማሳደግ፣

- በፌደራል ደረጃ በአረጋውያን ዙሪያ የተደራጁ ማህበራት ያላቸውን ክፍተት (ተግዳሮቶች) በመለየት ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ አፈጻጸማቸውን ማሳደግ፣
- አረጋውያን በዕውቀታቸው፣ በክህሎታቸው እና በተገቢ ልምዳቸው መሰረት በተለያዩ ተቋማት የማማከር አገልግሎት የሚሰጡበት የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣
- በአረጋውያን ዙሪያ የህብረተሰቡን እና የአስፈጻሚ አካላትን ሚና በተመለከተ በሥስትርዕሰ ጉዳዮች የግንዛቤ ጽሁፎችን በማዘጋጀት በተለያዩ የኮሚዩኒኬሽን ዘዴዎች ማሰራጨት፣
- ከኢትዮጵያ አረጋውያንና ጡረተኞች ብሔራዊ ማህበር ጋር በመተባበር አረጋውያን ያካበቱትን እውቀትና ክሎት ለትውልዱ ለማሸጋገር የሚያስችሉ 6 የዕውቀት ሽግግር መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- አረጋውያን በህይወት ዘመናቸው ለትውልዱ እና ለሀገር ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ለማስገንዘብተገቢውን ክብር እንዲያገኙ እንዲሁም የሚደርስባቸውን ችግር ለማወቅ እና ለመከላከል የሚያስችል አንድ የ25 ደቂቃ ዶክመንተሪ ፊልም በማዘጋጀት መገናኛ ዘዴዎች ማሰራጨት፣
- የሚድያ ተቋማት የአረጋውያንን ጉዳዮች ያካተተ ሚዛናዊ የሥርጭት ሽፋን እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል የግንዛቤ መፍጠሪያ አንድ የሥልጠና መድረክ ማዘጋጀት፣
- የአፍሪካ ሕዝቦችና ሰዎች መብቶች ቻርተር የአፍሪካ አረጋውያንን ፕሮቶኮል አዋጅ ቁጥር1182 /2012 እና Senior Citizen guideline በማስተዋወቅ ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ፣
- በፌደራል ደረጃ የአረጋዊያን የቅንጅት ፎረሞችን በማቋቋም አፈጻጸማቸውን በተመለከተ በአመት ሁለት ጊዜ በመገምገም ግብረመልስ መስጠት፤
- የአረጋዊያንን መሰረታዊ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎች የተመለከተ የመረጃ ቋት ( Data Base ) መመስረት
- ዕድሮች እና ተመሳሳይ የማህበረሰብ አደራጀቶች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ አረጋዊያንን ለመደገፍ የሚያስችል የአሰራር ጋይድላየን በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፤

## ግብ 5፡ የተሃድሶ አገልግሎቶችን በማስፋፋት አረጋውያን ተገቢውን ድጋፍ እና እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ

### ውጤት 1፡ የተዘረጉ የተሀድሶ አገልግሎቶችና የተቋቋሙ አረጋውያን

<u>የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

- ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ አረጋውያን በበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ውስጥ ተገቢውን ክብር፣ ድጋፍ እና እንክብካቤ ማግኘት የሚያስችል ፕሮጀክት ቀርጾ ተግበራዊ ማድረግ፣
- የአረጋውያን ብሔራዊ ድርጊት መርሀ-ግብር( ከ2014-2018) ከሴክተሩ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እና ከወቅታዊ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች አንጻር በመከለስ ማሻሻል፣
- በአረጋውያን ጉዳዮች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሥራ አፈጻጸም የሚገመግም እና አቅጣጫ የሚያስቀምጥ አንድ የጋራ የምክክር መድረክ ማካሔድ፣
- ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር እና ሀብት በማሰባሰብ ብሔራዊ ሁለገብ የአረጋውያን ማዕከል ግንባታ እንዲጀመር ማድረግ፣
- ለሚመለከታቸው አካላት ሥልጠና በመስጠት እና ድጋፍ በማድረግ አረጋውያን ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ መሰማራታቸውን ማረጋገጥ፣
- ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች (ሔልፕኤጅ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ እና ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን) ጋር የፕሮጀክት መግባቢያ ሰነድ የተፈጸመባቸውን ሰነድ ፕሮጀክት አፈጻጸምን መከታተልና መገምገም፣

## ግብ 6፡ የቅንጅት እና ትብብር ሥራዎችን በማጠናከር በተቋማት የኃላፊነት ክልል የአረጋውያንን ጉዳዮች ተፈጻሚነት ማረጋገጥ

### ውጤት 1፡ የተጠናከረ የቅንጅትና የትብብር ሥራዎች፣

<u>የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

- በአረጋዊያን ላይ የሚፈፀሙ የመብት ጥሰቶችን ለመከላከል፣ ጥሰት የተፈጸመባቸውም ተገቢውን የህግ ድጋፍ እንዲያገኙና መብቶቻቸው እንዲከበሩላቸው የተከናወኑ ተግባራትን በመገምገም ግብረመልስ መስጠት፣

- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማህበራዊ አገልግሎት ፕሮግራማቸው አረጋዊያን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራን እንዲያከናውኑ ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት በቅንጅትና ትብብር መስራት፣
- በጤና ሚኒቴር እና በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የተዘጋጀው የጤናማ አረጋዊነት ስትራቴጂ (ሄልዚ ኤጂንግ ስትራቴጂ) ተግባርን በመከታተል የአረጋውያንን ተጠቃሚነት የሚያሳይ መረጃ ማደራጀት፣
- ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ አረጋውያን ነጻ የህክምና እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኙ ከጤና ሚኒስቴር እና ከተራንስፖርት ሚኒኒስቴር ጋር በመተባበር የአሰራር ጋይድ ላይኖችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ ፣
- የሚዲያ ተቋማት ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ አረጋዊያንን በሥራዎቻቸው አካተው የሚሰሩበትና ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ከመወጣት አንጻር ያከናወኗቸውን ተግባራት በመምገም ግብረመልስ መስጠት፣

## ግብ 7፡ የአካል ጉዳተኞችን ተካታችነት፣ ተሳታፊነት፣ ተደራሽነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ

**ውጤት 1፡ ተጠቃሚ የሆኑ የአካል ጉዳተኞች፣**

<u>**የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**</u>

- የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ የሚከታተል በሁሉም የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና አደረጃጀቱን ባልፈጠሩ ክልሎች አደረጃጀት እንዲፈጠር በመከታታል በመደገፍ እንዲሁም በማብቃት የአካል ጉዳተኞችን የእኩል እድል ተጠቃሚነት እና ተሳታፊነት ማረጋገጥ፣
- የአካል ጉዳተኞችን መረጃዎች ወጥነት ባለው መንገድ ከፌዴራል እስከ ወረዳ አራጅቶ ለመያዝ የሚያስችል የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርአት በመዘርጋት ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ፍታዊነትና ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ማየት የተሳናቸውን ዜጎች የመረጃ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ፣ የቀረጥ ነፃ ተሸከርካሪ መመሪያ እና የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬሽንን በብሬል በማሳተም ለአይነ ስዉራን ዜጎች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣

- ❖ የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ እና ከመ/ቤቱ ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ውል የገቡ ድርጅቶች አፈጻጸማቸው በተያዘላቸው ጊዜና በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ተፈፃሚ ስለመሆናቸዉ በመከታተል በመቆጣጠር በመገምገም ግበረ መልስ መስጠት፣
- ❖ በመመሪያ ቁጥር 41/2007 አገልግሎቱን ለሚጠይቁ የእንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው አካል ጉዳተኞች ሁሉ የእንቅስቃሴ ችግራቸውን ለማቃለል ተሽከርካሪ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ለማስገባት እንዲችሉ የድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣
- ❖ የአካል ጉዳተኞችን የሥራ ሥምሪት አዋጅ በማሻሻል የአካል ጉዳተኞች የስራ መቀጠር እድል እንዲሰፋ እና የተመጣጣን ማመቻቸት ሁኔታ መሰረታዊ በሚባል ደረጃ እንዲሻሻል ማድረግ፣
- ❖ የተጠቃለለ የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ህግ (Ethiopian Disability Act) እና የአፍሪካ የአካል ጉዳተኞች ቻርተር ጸድቀው ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ፣
- ❖ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የኮሙኒኬሽን እና አድቮኬሲ ማኑዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣
- ❖ ለት/ት ሚ/ር፣ ለጤና ሚኒስቴር፣ ለሳይንስና ከፍተኛ ት/ት ሚ/ር፣ ለፌደራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ፤ ለፌደራል የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኮሚሽን፣ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር እና ለትራንስፖርት ሚ/ር ከአካታችነትና ተደራሽነት አንፃር ኃላፊነትና ሚናቸውን የሚዘረዝር አንድ ሰነድ ማዘጋጀትና ማስተዋወቅ፣
- ❖ በክልሎች አካል ጉዳተኞችን የሚመለከት ሥራዎች ያሉበትን ደረጃ፣ ከቢሮ እስከ ወረዳ ባሉት እርከኖች የሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶች፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶችና የአገልግሎት ጥራትን በተመለከተ በተመረጡ ሁለት ክልሎች የመስክ ምልከታ በማድረግና በመመካከር የማሻሻያ ግብረ-መልስ መስጠት፣
- ❖ በአካል ጉዳተኞች ላይ ለመሥራት ከመንግስት ፈቃድ የወሰዱ እና ከአንድ ክልል በላይ የሚሰሩ 4 ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ሥራ የመስክ ምልከታ በማድረግና በመመካከር የማሻሻያ ምክረ-ሃሳብ መስጠት፣
- ❖ ለፌደራል አስፈጻሚ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የተ.መ. ድ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አፈጻጸም በሚመለከት አንድ ጊዜ ክትትልና ድጋፍ ሥራን በማከናወን እና ግብረ መልስ መስጠት፣

- የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትናን አስመልክተው የሚሰሩ ሥራዎች ምን ያህል አካል ጉዳተኞችን አካታች እንዳደረጉና የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንደሆኑ በአዲስ አበባና በሌሎች 2 የክልል ከተሞች የመስክ ምልከታ በማድረግና በመመካከር የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ እንዲረዳ ግብረ-መልስ መስጠት፣
- ከመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ሆስፒታሎች፣ የቴ/ሙ.ያ ስልጠና ኮሌጆች፣ የብድርና ቁጠባ ተቋማትና ባንኮች አንድ አንድ በመምረጥና የመስክ ምልከታ በማድረግ የአካታችነትና የተደራሽነታቸውን ሁኔታ በመፈተሽ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር አስፈላጊው የማሻሻያ እርምጃ እንዲወሰድ ምክረ ሀሳብ መስጠት፣
- የሚመለከታቸውን አካላት በማተባበር ለአካል ጉዳተኞች የሰው ሠራሽ የአካልና የአካል ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- 15,000 የሚሆኑ አካል ጉዳተኞች፣ በሲቪክ ማህበራት የድጋፍ እና የእንክብካቤ እንዲያገኙ የቁጥጥር፣ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፣
- በሁሉም የተሃድሶ ማዕከላት ዉስጥ ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጡ አገልግሎቶች ጥራት እንዲሻሻል በጤና ሚኒስቴር የተዘጋጀው የተሀድሶ ጋይድላይን ተግባራዊነትን መከታተል መደገፍና የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ግብረ መልስ መስጠት፣
- በድህነት እና በተጋላጭነት ውስጥ የሚገኙ አካል ጉዳተኛ ዜጎች በዝቅተኛ ክፍያ የሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፎችን እንዲያገኙ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በመመርያ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው ለሚቀርቡ የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው አካል ጉዳተኞች በቀልጣፋ ሁኔታ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ የተሽከርካሪ አገልግሎት የድጋፍ ትብብር እንዲያገኙ ማስቻል፣
- የልማት አጋሮችን በማስተባበር 2,000 የአካል ድጋፎችን በማሰባሰብ የመግዛት አቅም ለሌላቸው እና የድሀ ድሀ ለሆኑ በገጠር ለሚገኙ አካል ጉዳተኞች ተደራሽ ማድረግ፣
- በተሃድሶ ማእከላት የማህበራዊ ተሃድሶ አሰጣጥ የአሰራር ጋይድላይን ማዘጋጀትና በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣
- ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ አገልግሎት የሚሰጡ በፌደራል ደረጃ የሚገኙ የተሃድሶ ማእከላትን ቅንጅታዊ አሠራር ለማጎልበት የሚያስችል አንድ የጋራ ፎረም በማቋቋም አገልግሎት አሰጣጡን ማጠናከር፣

- ❖ ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ተገቢ ሚናቸውን እንዲወጡ በዓመት ሁለት ጊዜ የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ የአካል ጉዳተኞች ማህበራትን አቅም በመገንባት እና በማጠናከር የሚሰጡ አገልግሎቶችን ማሻሻል፣
- ❖ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የት/ት መርጃ መሣሪያዎች ለማሟላት፣ ለችግር ለተጋለጡ አካል ጉዳተኞች ማህበራዊ ድጋፍ፣ ለአካል ጉዳተኞች ማህበራት እና ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሠራተኞች የአቅም ግንባታ እና ለ10 ዓመቱ የድርጊት መርሃ ግብር ሰነድ ዝግጅት እና ለአካል ጉዳተኞች የሥራ ሥምሪት አዋጅ ማሻሻያ የሚሆን ስድስት ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን ቀርጾ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በማቅረብና ሀብት በማሰባሰብ ሥራ ላይ በማዋል ተቋማዊ አቅምን መገንባት፣
- ❖ በብሄራዊ ደረጃ የተደራጁ 9 የአካል ጉዳተኛ ማህበራትን መደገፍና ማጠናከር፣
- ❖ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በተለያዩ የሥራ መስኮች መሳተፍ ከሚችሉ 616,154 ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ አካል ጉዳተኞች የትምህርት፣ የስልጠና እና የሥራ ስምሪት ዕድል እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ❖ ማህረሰብን መሠረት አድርገው የተዋቀሩ 38,947 አደረጃጀቶች፣ ሲቪክ ማህበራት እና የንግዱ ማህረሰብ ለአካል ጉዳተኞች የድጋፍ እና የእንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ በማድረግ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣
- ❖ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር 62,160 የአካልና የአካል ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ❖ ተከታታይነት ያላቸው በየዓመቱ የሥልጠናና የግንዛቤ ማሳደጊያ 9,928 መድረኮችን በመፍጠር ህብረተሰቡ ለአካል ጉዳተኞች እንክብካቤ እንዲሰጡ ማስቻል፣
- ❖ ለ3,100 የአካል ጉዳተኞችን የምክር (Guidance) እና የምክክር (Counseling) አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፣
- ❖ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር እና በመምራት ለ1183 አካል ጉዳተኞችን የኪነ-ጥበብና የስፖርት ተሳትፏቸውን ማሳደግ፣
- ❖ ለ1,812 ሚቋቋሙ አዲስ የአካል ጉዳተኛ ማህበራት እንዲቋቋሙ ድጋፍ ማድረግ
- ❖ ለ2,811 ነባር አካል ጉዳተኞች ማህበራት እንዲጠናከሩ ድጋፍ ማድረግ፣

**ግብ 8፡ የሴክተሩ ሙያተኞችና በዘርፉ የሚንቀሳቀሱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ብቁ በማድረግ የሴክተሩን ተልዕኮ ማሳካት፣**

**ውጤት1፡ ተደራሽነቱ ያደገ የማህበራዊ ጥበቃ አገልገሎቶችን፤**

<u>የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

- በሀገሪቱ የሚገኙትን የማህበራዊ ዘርፍ ስልጠና የቴክኒክና ሙያ የማሰልጠኛ እና የመመዘኛ ተቋማት አቅም፣ የገበያ ፍላጎት እና ሁኔታ የሚያሳይ የዳሰሳ ጥናት እያጠና ያለውን የአማካሪ ድርጅት ሥራውን በተገቢው መንገድ እንዲያከናውን በፌደራል ደረጃ ከተቋቋመው ብሔራዊ ኮሚቴ ጋር በመተባበር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

- ከፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በማህበራዊ ዘርፍ ካሪኩለም ከተቀረጸላቸው 6 ዘርፎች መካከል የኮምዩኒቲ ሰርቪስ ወርክ እና የሶሻል ወርክ ሙያዎችን ካሪኩለም መከለስ፣ የምዘና መሣሪያዎች ማዘጋጀት እና ለቴክኒክና ሙያ ተቋማት አሰልጣኞች የማስተማር ስነ ዘዴ ላይ ሥልጠና መስጠት፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከዩኒሴፍ ጋር በመተባበር የቀጠረው አማካሪ ድርጅት (በሀገሪቱ የሚገኙትን የማህበራዊ ዘርፍ ስልጠና የቴክኒክና ሙያ የማሰልጠኛ እና የመመዘኛ ተቋማት አቅም፣ የገበያ ፍላጎት እና ሁኔታ የሚያሳይ የዳሰሳ የጥናት) የሚያጠናውን የጥናት ውጤት መሰረት በማድረግ በአገሪቱ በማህበራዊ ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ባለሙያዎችን ብቃት የሚያረጋግጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ የሚያግዝ አንድ ጋይድ ላይን እንዲያዘጋጅና ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣

- በአገሪቱ በማህበራዊ ዘርፍ ተሰማርተው ለሚገኙ በለሙያዎች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል አንድ ጋይድ ላይን እንዲዘጋጅ እና ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣

- አንድ መድረክ በማዘጋጀት በክልልና በወረዳ ለሚገኙ በማህበራዊ ዘርፍ ሥራ ላይ ለተሰማሩ የማህበራዊ ባለሙያዎች Strengthening Social Service System in Ethiopia ዳታ ቤዝ አጠቃቀም ላይ ሥልጠና መስጠት፣

## ዋና ዋና አስተዳደራዊ ስራዎች

### የህግ ድጋፍ አገልግሎት  መስጠት

የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብት ከማስከበር አኳያ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የህግ ምክር ፈልገው ወደ ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ለሚመጡ የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የህግ ምክር የመስጠትና አስፈላጊውን ድጋፍ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

### የተቋሙን ፋይናንስ አጠቃቀምን ማሳደግ

ለተቋሙ የተበጀቱ የመደበኛ እና የተራድኦ በጀቶችን ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ለታቀደላቸው አላማ ብቻ እንዲዉል በማድረግ የፋይናንስ አጠቃቀምን የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በበጀት ዓመቱ የተያዙን ግቦችን እና ዉጤቶችን ለማሳካት በሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ዙሪያ የተለያዩ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀት እና ሃበት በማሰባሰብ የጠቋሙን የፋይናንስ አቅም የማጎልበት ስራ ይሰራል፡፡ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የመደበኛ በጀት እና የተራድኦ በጀትን በመጠቀም እቅዱን ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የፋይናንስ አሰራርን የማዘመን እና ክፍያዎች እና ግዢዎች የመንግሰትን ደንብና መመሪያ ብቻ ተከትለው እንዲፈፀሙ የሚደረግ ሲሆን ወቅቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት በማዘጋጅት ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

### የእቅድ ትግበራ ስራ አመራር ስርዓትን ማሳደግ፤

የተዘጋጀውን የሴክተር የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ከየክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች በወቅቱ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንዲልኩ በማድረግ በመገምገም የሩብ ዓመት፤የ 6 ወር፤የ 9 ወር እና ዓመታዊ የሴክተር ሪፖርቶችን በናበመገምገም ሃገራዊ የሴክተር ሪፖርት በወቅቱና በጥራት በማዘጋጀት ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፣ ለፕላንና ልማት ኮሚሽን፣ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለአካባቢ፤ደንና የአየር ንብረት ለውጥ እንዲሁም የበጀት አፈጻጸም ተግባራትን ለፋይናንስ ሚኒስቴር በወቅቱ የሚላክ ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ

በክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች የተከናወኑ ተግባራትን መሰረት በማድረግ በየሩብ ዓመቱ የመስክ ድጋፍና ክትትል የሚደረግ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም የፕሮግራም/ፕሮጀክቶች ስራዎችን ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር በመሆን እቅድ ማዘጋጀትና ስራዎች በተቀመጠላቸው ጊዜ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማስተባበር፣ መከታተል መደገፍና የግምገማና የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ዙሪያ የመስክ ክትትል ማድረግና ግብረ-መልስ መስጠት፣ እንዲሁም አፈፃፀም ዙሪያ ዓመታዊ የግምገማ መድረክ ማካሄድ፣

## የመረጃ ፍሰት በማዘመን ተደራሽነትን ማሳደግ

የሴክተሩን የመረጃ ፍሰትና ተደራሽነት በማጎልበት በሴክተሩ ስራዎች ላይ ባለድርሻ አካላት እና ማህበረሰቡ በቂ ግንዛ እንዲያገኙ ለማድረግ የተቋሙን የውስጥና የውጭ ግንኙነት የማጠናከር፣ የሴክተሩን ስራዎች ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃዎች በተገቢው ሁኔታ የሚያሳዩ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን፣ የጋዜጣ አምድ፤በራሪ ፅሁፎችን፣ ዶክዩመንታሪ ፊልሞችን እና መጽሄቶችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ተደራሽ የማድረግ ስራዎች ይሰራሉ፡፡

የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ዙሪያ በክልልች ላይ የሚገኙ መረጃዎችን በመረጃ ቋቶች (ዳታ ቤዝ) በማደራጀት ጥቅም ላይ ለማዋል የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የመረጃ ቋቶች በማበልፀግ ወደ ስራ የማስገባት እንዲሁም የወጣቶቸን መረጃ ቋት የመመስረት ስራዎች ይሰራሉ፡፡

የተቋሙን የአሰራር ስርዓት በማዘመን ወረቀት አልባ የማድረግ እንዲሁም በተቋሙ እና ባለድርሻ አካላት የሚደረጉ የመረጃ ልውውጦችን የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተቋሙን የሰው ሃይል መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ሊይዝ የሚችል የመረጃ ቋት የመመስረት እና የመዝገብ የመረጃ አያያዝና አሰራር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ለማድረግ ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋት ስራ ይሰራል፡፡ ከነዚህም መካከል የወጣቶች ዳታቤዝ ማዘጋጀት፤የስርዓተ-ጾታ የመረጃ ቋት (National Gender Information System-NGIS) ተግባራዊነት ማረጋገጥ፣

## የሰው ሃብት ልማትን ማጎልበት

በበጀት ዓመቱ በሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ በጥናቱ የተያዘውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በጥናቱ መሰረት የሚያስፈልግ የሰው ሃይል እንዲሟላ ይደረጋል፡፡ በበጀት ዓመቱ ስራውን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል የማሟላት ስራ ይሰራል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለሰራተኛው የተለያዩ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት/በማመቻቸት የባለሙያዎችን እና አመራሮችን አቅም በመገንባት በበጀት ዓመቱ የታቀዱ ተግባራትን በብቃት ለመወጣት ተከታታይነት ያላቸው የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተዘጋጀውን የሰው ሀብት ስትራቴጂ ለተቋሙ ሰራተኞችና አመራሮች ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ትግበራ እንዲገባ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

## የህዝብ ግንኙነት፣ ኮሙኒኬሽን ሥራዎችንና የመረጃ ፍሰትን ተደራሽነትን ማሳደግ፣

የመስሪያ ቤቱን ተግባራት የሚያስተዋውቁ ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃ የያዙ የህትመት ውጤቶችን ማዘጋጀትና ተደራሽ ማድረግ፣የፎቶ ግራፍና ኢዲዮቪዥዋል ስራዎችን መስራት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚካሄዱ ሁነቶች በህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች እንዲደገፉ ማድረግ፣ ሚድያ ደሳሳ ማድረግ፣ የተቋሙን የውስጥና የውጭ ግንኙነት ማጠናከር እና የሴክተሩን የመረጃ ምንጮች ቁጥር ማሳደግ፣ የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ጉዳዮች ዙሪያ የለውጥ ኮሚኒኬሽን (የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራም የአየር ሰዓት በመግዛት የጋዜጣ አምድ፤ዶክዩመንታሪ ፊልም መጽሄቶችን… ወዘተ) በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ፣የመረጃ መስጫ ፕላዝማ በመጠቀም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የኮሙኒኬሽን ስራዎችን መስራት፣ በፌስቡክ በቴሌግራም በትዊተር እና በመሳሰሉት ድረገጾች ወቅታዊ መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ፣

## የኦዲት አገልግሎት ማከናወን

የመ/ቤቱ የፋይናንስና ንብረት አጠቃቀም መንግስት የሚያወጣቸውን ደንብና መመሪያዎች በማዕከላዊነት የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣የክዋኔ ኦዲት ማካሄድ፣ ወቅቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት በማዘጋጅት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፣

## የሪፎርም ሥራን መከታተልና መገምገም፣መደገፍ

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የለውጥ ሠራዊት ግንባታ ሥራን አጠናክሮ ለማስቀጠል በተለያዩ ርዕሶች ላይ ሥልጠናዎችን መስጠትና ፋይዳውን መገምገም፣ከለውጥ ሠራዊት የህዝብ ክንፍ ጋር የውይይት መድረክ ማካሄድ፣የዜጎች ቻርተር አፈጻጸም ላይ ሱፐርቪዥን ማካሄድ፣ የሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም ምዘና እንዲካሄድ ማድረግ፣ በቲም ቻርተሩ መሠረት ተግባራት ይገመገማል፣የተገልጋይ እርካታን ለማረጋገጥ መስራትና መስፈርቶቹን መገምገም፣ በኪራይ ሰብሳቢነትና መልካም አስተዳደር ዙሪያ ችግሮቹን ለመቅረፍ በዕቅድ መስራት፡፡

## የሥነ ምግባር እና ጸረ - ሙስና ተግባራትን መከታተል

የሥነ ምግባርና ጸረ  ሙስና ጉዳች ዙሪያ ለሰራተኞች ግንዛቤ መፍጠር፣የሥነ ምግባርና ሙስና  ችግሮችን መከላከልና መፍታት፣ከህግ ዳሬክቶሬት፣ ከሰው ሃብት ዳሬክቶሬትና ከሪፎርም ዳሬክቶሬት ጋር በመሆን ሚንስተር መስርያ ቤቱን በሚመለከቱ ደንቦችና መመርያዎች ላይ ስልጠና መስጠት፣

## የንብረት አቅርቦትና የጠቅላላ አገልግሎት ድጋፍ መስጠት

የተቋሙን ንብረት ከግዢ ጥራትና በስፔሲፊኬሽኑ መሰረት መግባት ጀምሮ  ንብረቱ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ስራ መስራት፣በመንግስት ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም ደንብና መመሪያ መሠረት ለተሽከርካሪዎች የነዳጅ የኢንሹራንስና የተለያየ መኪና መለዋወጫ እቃዎች ግዥ የሚሆን በጀት እንዲያዝ ማድረግ ፣በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን መቆጣጠር ፣በተያዘው በጀት መሰረት ግዥ ስለመፈጸሙ ክትትል ማድረግ፣ የመኪና ጥገና ውሎችን ከሚመለከት የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን የጥገናና ዕድሳት የውል ሰነድ ማዘጋጀት ፣ጥገና ለሚያስፈልጋቸው የተቋሙ ቋሚ ንብረቶች ቅድመ ጥናት ማድረግ፣ የግቢውን ደህንነት፣ ጽዳትና ውበት  መጠበቅ፣ የተደራጀና ዘመናዊ የጥበቃ አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ አፈጻጸሙን መከታተላል፣ መገምገም እንዲሁም ፍትሃዊ የትራንስፖርት ስምሪት አገልግሎት መስጠት፣ ለሰራተኞች ለስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች የማቅረብና አጠቃቀማቸውን የማሳወቅ ስራ ይሰራል፡፡

## የእቅዱ ማስፈጸሚያ ስልቶች

- የሚኒስቴር መ/ቤታችን ስራዎች በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በባህሪያቸው የግንዛቤና ንቅናቄ መድረኮችን የሚይጠይቁ፣ በአካል ሙያዊ ድጋፍ መስጠትና የክትትል ስራዎችን የሚጠይቅ እንዲሁም በአጠቃላይ በሀገሪቱ በገጠርና በከተማ የሚኖሩትን ማህበረሰብ በአንድ ቦታ መሰባሰብ የሚጠይቁ በመሆናቸው በ2013 በጀት ዓመት በኮሮና ቫይረስ በሽታ ስርጭት ምክንያት ከዚህ በፊት ስንከተላቸው የነበሩ የማስፈፀሚያ ስልቶች ተግባራዊ ለማድረግ በከፊል አስቸጋሪ በመሆኑ ከዚህ በታች የሚተገበሩና አዳዲስና ከወቅቱ ጋር የሚሄዱ ስልቶች ቀርበዋል፡፡
- የቴክኖሎጂ ውጤቶችን (zoom, skype, telgeram, facebook, email, electronics survey tools, etc...) በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን፣ ድጋፍና ክትትሎች፣ ጥናትና ምርምሮችን፣ ቀጥታ አገልግሎቶችን እና ሌሎች ተግባራት መፈፀም የሚቻልበትን ስልት መቀየስ፣
- የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እንዲሁም በበጀት ዓመቱ የሚሰሩ ስራዎችን እና የተደረሰባቸውን የአፈጻጸም ደረጃዎች ለሁሉም ባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮች የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ተደራሽ ማድረግ፣
- ከፌዴራልና ከክልል ሴክተር መ/ቤቶች ጋር የተለያዩ ስልቶችን በመቀየስ ከእቅድ ዝግጅት እስከ ትግበራ ድረስ ስራዎችን በትብብርና በቅንጅት መስራት፣
- የወቅቱን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ የክትትልና የግምገማ ስርአት በመዘርጋት የበጀት ዓመቱን እቅድ አፈጻጸም ደረጃ ማሻሻልና ውጤታማነትን የማጎልበት ስልት መቀየስ፣
- የክልሎችንና የአደረጃጀቶችን አቅም ማጎልበት፣ እቅዱ መሬት ላይ ወርዶ በተጨባጭ በሴቶች ላይ ውጤት በሚያመጣ መልኩ እንዲተገበር ክልሎችን፣ ሴክተር መ/ቤቶችንና አደረጃጀቶችን በእቅዱና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ አቅማቸውን በመገንባት እቅዱን በባለቤትነት እንዲያስፈጽሙት ማድረግ፣
- መረጃዎችንና ጥናቶችን ተደራሽ በማድረግ የታቀዱ ተግባራት መረጃን መሰረት አድርገው እንዲተገበሩ ለማድረግ የጥናትና ምርምር ስራዎች እና መረጃዎችን በማደራጀት ፣ በመተንተን ለሚመለከተው አካል ጥቅም ላይ እንዲያውላቸው ማድረግ፡፡

## የክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ግብረ መልስ ስርአት

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሁሉም ዘርፍ በየደረጃው የሚከናወኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፤ በሴክተሩ ግቦችና ውጤቶች፣ በሴክተር መ/ቤቶች፣ የሴቶቸ፤ወጣቶችና ህጻናት አደረጃጀቶች ፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የግሉ ዘርፍ ወዘተ. የሚከናወኑ ስራዎች በአሰራርና አደረጃጀት የተደገፈ ጠንካራ የክትትል፣ የግምገማና ግብረ መልስ ስርዓት የሚዘረጋ ይሆናል፡፡ በዚህ ሂደትም የሚመለከታቸው አካላት ማለትም የክልል ቢሮዎች፣ የህብረተሰብ አደረጃጀቶች፣ አጋር የልማት ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የተፈጠሩ ልዩ ልዩ የቅንጅትና ትብብር ፎረሞች ለስራው ስኬት ትርጉም ባለው መልኩ የሚሳተፉበትን ሁኔታ የሚፈጠር ይሆናል፡፡

በመሆኑም በዘርፉ በበጀት ዓመቱ የተቀመጡ አመላካቾችን ወሳኝ ድርሻ ካላቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የልማት ፕሮግራም ጋር እንዲጣጣሙ የሚደረግ ሲሆን ለዝርዝር ትግበራው የራሱ የሆኑ የድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት አፈፃፀሙ የደረሰበትን ደረጃ በተቀናጀ የክትትልና ግምገማ ስልት በየጊዜው የሚለካ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በሴክተሩ በበጀት ዓመቱ በተሟላ መልኩ ለማሳካት የህጻናት መብትና ደህንነት ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የሚከተሉት ዋና ዋና አጀንዳዎች በቅደም ተከተላቸው የሚፈፀሙ ይሆናል፡፡

- የተቀናጀና አሳታፊ የእቅድ ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ መልስ ስርዓት ይዘረጋል፣
- ከላይ እስከ ታች የተናበበና ወጥነት ያለው እቅድ በማዘጋጀት በእቅዱ ዙሪያ በዘርፉ እና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ዘንድ ተገቢውን ግንዛቤ ተይዞበት ወደ ትግበራ እንዲገባ እንዲሁም የጋራ አመለካከትና የባለቤትነት መንፈስ እንዲዳብር ይደረጋል፣
- የእቅዱ አመላካቾች ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የልማት ፕሮግራሞች ጋር እንዲጣጣሙ በማድረግ ለክትትልና ግምገማ አመቺ በሆነ መልኩ የራሱ የድርጊት መርሀ ግብር እንዲዘጋጅለት ይደረጋል፣ አፈፃፀሙም በየጊዜው ይገመገማል፤
- በረዥም ጊዜ እቅዱ የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ ወደ ክልሎች/የከተማ መስተዳደሮች በተጣጣመ መልኩ እንዲወርድ ድጋፍ ይደረጋል፤ አፈፃፀሙ ላይም የተቀናጀ ክትትልና ግምገማ ይካሄዳል፡፡

- የእቅድ ዝግጅትና ትግበራው ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ክልሎች የሚደረግ ልዩ ድጋፍን ባገናዘበ መልኩ የሚተገበር ይሆናል፡፡
- የበጀት ዓመቱ እቅድ በዓመት፣ስድስት ወር፣ በሩብ ዓመት እየተሸነሸነ የሚተገበር ይሆናል፡፡

## ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችና ሊወሰዱ የሚገባቸው መፍትሄዎች፣

### መልካም አጋጣሚዎች

- ❖ የሴቶች አደረጃጀቶች ቅንጅታዊ አሰራር እየተጠናከረ መምጣቱና የማስፈጸም አቅማቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ መምጣቱ፣
- ❖ በየደረጃው የመንግስት አካላት ለሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት የሚሰጡት ትኩረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ ፣
- ❖ የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን አፈጻጸም የሚከታተልና የሚቆጣጠር አካል(ካውንስል) በየደረጃው መቋቋሙና የተጠያቂነት ስርዓት እየጎለበተ መምጣቱ፤
- ❖ የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እና እየተስፋፋ መምጣቱ፡፡
- ❖ ከአጋር አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ ስራ እየተጠናከረ መምጣቱ፤

## ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች/ ስጋቶች

- ❖ እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ወጥ የሆነ የሴክተር መዋቅር አለመኖር፤
- ❖ ከልማት እቅዱ ስፋት አንፃር የፋይናንስና ግብዓት ውስንነት ሊያጋጥም ይችላል፤
- ❖ እንደ ተቋምም ሆነ በአጋር አካላት ለዘርፉ የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን፤
- ❖ ኮቪድ-19ን ጨምሮ ሰዉ ሰራሽና ተፈጥሯዊ ክስተቶች አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፤
- ❖ በሴክተሩ የሚጠበቀውን የልማት ፍላጐት ለማሳካት ተመጣጣኝ የሆነ ሰብዓዊ ሀብት ተሟልቶ ያለመገኘት፤

❖ ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች የሴክተሩን ልማት ለማፋጠን የሚጠይቀውን የተለየ ትኩረትና ድጋፍ ለመስጠት የአቅም ውስንነት መኖር፤
❖ የመረጃ ስርዓት ክፍተት መኖር፤

## መወሠድ ያለባቸው እርምጃዎች፡

❖ እስከ ታች ድረስ ወጥ የሆነ የሴክተር መዋቅር እንዲኖር በአመራሩ በኩል ጥረት ይደረጋል፤
❖ ጠንካራ የለውጥ ስሜትን በመገንባት ያለውን ሠራተኛ እያበቁ አዳዲስ ሠራተኞችን በማሟላት እቅዱን መፈፀም፣
❖ በሴክተሩ የሚገኘው አመራር የአመለካከትና የክህሎት ችግሮቹ የሚቀረፉበትንና በአመራር ሂደት የአመለካከት አንድነቱ፣ የሥራ ተነሳሽነቱና ቁርጠኝነቱ ወደ ተመሳሳይ ደረጃ እንዲመጣ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓቱን አጠናክሮ መቀጠል፤
❖ የተለያዩ አቅም ግንባታ ሥራዎችን በመሥራትና የክትትል፣ ወቅቱን የጠበቀ የግምገማ የድጋፍና፣ የሪፖርት ሥርዓቱን በማጠናከር የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ፤
❖ የተለያዩ የግንዛቤ ስራዎችን በማከናወን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በየደረጃው በመቅረፍ፤
❖ የተለያዩ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች በማዘጋጀትና ለተራድኦ ድርጅቶች በማቅረብ ሀብት የማፈላለግ ስራዎች በመስራት፤
❖ የመንግስትን ውስን ሀብት በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል የህዝብ ተሣትፎን ማጎልበት፤

## ማጠቃለያ

የሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ደሃና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሣትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና የህፃናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ፣ በበጀት ዓመቱ የልማት ዕቅድ የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት በበጀት ዓመቱ የተለያዩ የአሰራር፣የአቅም ግንባታ፣ የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎችን በመስራት ያለንን የሰው ኃይል አቅም አሟጠን በመጠቀም ዕቅዳችንን ለማሳካት ያላሰለሰ ጥረት እናደርጋለን፡፡